ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ-ምረቃ ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል


# በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ትንተና (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


በ

ቢራራ ደሴ



ነሐሴ, 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# የድህረ-ምረቃ ትምህርት

## የአማርኛ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ትንተና (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ

ቢራራ ደሴ

ዋና አማካሪ

ምህረት ሳዳሞ ዶ/ር

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሐ ግብር የአርት ማስተርስ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናታዊ ጽሑፍ

ነሐሴ, 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

## የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ________________ |

| ፈታኝ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ________________ |
| ______________________ | ________________ |

**ማረጋገጫ**

በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ትንተና የሚለው ጥናት እና ምርምር የራሴ የግል ሥራየ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ቢራራ ደሴ

ፊርማ --------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ከብዙ ነገር በቸርነቱ ጠብቆ ከዚህ ያደረሰኝ የድንግል ማርያም ልጅ፣ የፍቅር አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው፡፡ ከምንም በላይ ከጅማሬ እስከ ፍፃሜ ድረስ ጥናቱን ፈር በማስያዝ ብቻ ሳይወሰኑ ጥቃቅን ስህተቶቼን ሳይቀር በማረምና በማስተካከል ሙያዊ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ እንዲሁም በማበረታታት እዚህ ላደረሱኝ አማካሪዬ ዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ምስጋናዬ ይድረስ፡፡ በመቀጠልም በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ከጎኔ ላልተለየችኝ ለመምህርት ዚነት ሀሰን (መቅደስ) ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ይድረሳት፡፡እንዲሁም ለልጆቸ ናርዶስ ቢራራ እና ኑጎሚን ቢራራ ከልብ የመነጨ ምሥጋና ይድረሳቸው፡፡

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከትና አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መዳሰስ ሲሆን ተሳታፊዎችም በፊዴ ሁተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ አፋቸውን በሸኮኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተማሪዎቹ አመለካከት በሁለተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ማለትም በጽሑፍ መጠይቅና በፈተና መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በዚህም 52 ተማሪዎች በጥናቱ የተሳተፉ ሲሆን ለአራት ሳምንት የግንዛቤ ትምህርት ከተሰጣቸው በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በተመሳሳይ መልኩ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም በድህረ ጽሑፍ መጠይቅና የቅድመ ጽሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህም ተማሪዎች የነበራቸው ዝቅተኛ አመለካከት ወይም አሉታዊ አመለካከት ተቀይሮ አዎንታዊ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ዝቅተኛ የነበረው ውጤታቸው መሻሻሉን አሳይቷል፡፡

# ማውጫ

ርእስ ገጽ

ምስጋና....................................................................................................I
አጠቃሎ....................................................................................................II
ማውጫ.................................................................................................... iii
የሰንጠረዥ ማውጫ ....................................................................................................v
ምዕራፍ አንድ....................................................................................................1
መግቢያ....................................................................................................1
1.1. የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................1
1.2. አመለካከት ....................................................................................................1
1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................................................................3
1.4. የጥናቱ ዓላማ ....................................................................................................3
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ....................................................................................................4
1.6. የጥናቱ ወሰን....................................................................................................4
1.7 የጥናቱ ውሥነት ....................................................................................................4
1.8 የጥናቱ ጥያቄዎች ....................................................................................................4
1.8.1 የጥናቱ መሪ ጥያቄ .................................................................................................... 4
1.8.2 የጥናቱ ንዑሣን ጥያቄዎች.................................................................................................... 4
ምዕራፍ ሁለት....................................................................................................5
የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት....................................................................................................5
2.1. የአመለካከት ምንነት....................................................................................................5
2.2. አመለካከትን የማጥናት አስፈላጊነት....................................................................................................8
2.3. አመለካከት በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ ....................................................................................................9
2.4. ለአመለካከት መፈጠርና መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች....................................................................................................11
2.5. ቋንቋንና የቋንቋ ትምህርትን አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት እና ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች....................................................................................................14
2.5.1. ጓደኛ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ .................................................................................................... 14
2.5.2. ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች.................................................................................................... 17
2.5.3. የመምህሩ ስብዕናና የማስተማሪያ ዘዴው.................................................................................................... 19
2.5.4. መማሪያ መፃህፍት .................................................................................................... 21

2.6. የአመለካከት መለኪያ ዘዴዎች........23
2.7. የቀደምት ስራዎች ቅኝት........24
ምዕራፍ ሦስት........26
የጥናቱ ንድፍና ዘዴ........26
3.1. የጥናቱ ንድፍ........26
3.2. የመረጃ ምንጮች........26
3.3. የናሙና አመራረጥ........27
3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ........27
3.3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ........27
3.3.3. የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ........27
3.3.4. የጽሁፍ መጠይቅ........28
3.3.5. ፈተና........28
ምዕራፍ አራት........29
4.1.የመረጃ ትንተና የውጤት ማብራሪያ........29
4.1.1. የቅድመ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና........29
4.1.2. ከድህረ ትምህርት የተገኙ መረጃዎች ትንተና........29
4.1.3. የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተናና ልዩነት በዳግም ልኬት ናሙና........30
4.1.4. የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ........31
4.1.5. ከቅድ ት.ምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና........34
4.2. የውጤት ማብራሪያ........40
ምዕራፍ አምስት........43
5.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች........43
5.1.ማጠቃለያ........43
5.2.የመፍትሄ ሀሳቦች........44
ዋቢ ጽሑፎች........47
አባሪዎች........51
አባሪ አንድ........51
አባሪ ሁለት........66
አባሪ ሦስት........67
አባሪ አራት........68

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ-2 ከቅድመ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤትና ልዩነት....29

ሰኝጠረዥ 3 ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤትመደበኛ ልይይት.30

ሠንጠረዥ 4 የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና የአመለካካት መሻሻል በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት........................................................................................30

ሰንጠረዥ 5 ከቅድመ ትምርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ................................32

ሰንጠረዥ 6› ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኝ የውጤት ድግግሞሽ....................................33

ሰንጠረዥ 7. በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ .............34

ሰንጠረዥ 8 ከቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ..................34

ሰንጠረዥ 9 በድህረ ት/ት በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና .............................36

ሠንጠረዥ 10፡- የቅድመ እና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት.........................................................................................................40

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

### 1.2. አመለካከት

አመለካከት የሚማሩትና በልምድ የሚያዳብሩት እምነት ወይም አተያይ ነው፡፡ ይህም ሲባል አመለካከትን የሚማሩት ከደም ጋር የተዋሀደና አብሮ የበቀለ ሳይሆን በልምድና በትምህርት የሚገኝ ነው፡፡ የአንድ ሰው አንድን ነገር የመውደድና የመጥላት ባህሪያት የሚዳብሩት በሚገጥሙት የተለያዩ ሁኔታዎች መነሻነት ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥም ምንም እንኳን ተማሪው በመጀመሪያ ጥሩ አመለካከት ወይም ከሁሉም ገለልተኛ የሆነ ግምት ይዞ ቢቀርብ በክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በሚገጥሙ ነገሮች አመለካከቱ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ይህም ሲባል አመለካከት በሚገጥሙት ነገሮች ሊለወጥ፣ ሊዳብርና ሊሻሻል ይችላል ማለት ነው፡፡ ማለትም የአመለካከት ባህሪው ሁኔታዊና ተለዋዋጭም ነው፡፡

Gagne (1976) እንደገለጹት የሰው ልጆች በአጠቃላይ ለነገሮች ወይም ለክስተቶች የሚኖራቸው በጎ ወይም በጎ ያልሆነ አተያይ አመለካከት ነው፤ ይላሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር Morgan (1986:382-384) ሲገልጹ በግለሰቦች ገለጻ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለአንድ ነገር የሚሰጡትን ግምገማ የሚወክል ነው፡፡ በመቀጠል ማንኛውም ግምገማ ስሜት የሚቀሰቅስ ነገር ለአንድ ሁኔታ ወይም ነገር አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ይህም ለአንድ ነገር የሚኖረን ግምት የመውደድ፣ የመጥላት፣ የመደገፍ፣ የመንቀፍ የመስማማት ያለመስማማት ሁነቶች አዎንታዊና አሉታዊ በሆኑ ምላሾች ይገልጻሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በFasold (1984፡147) አገላለፅ አመለካከት ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ምክንያትን ለአንድ ነገር የሚኖራቸው አተያይ ወይም ስሜት ነው፡፡ በሌላ በኩል ሰዎች ከማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ቀስቃሽ ሁኔታዎች ተነስተው የሚሰጡት ወይም በተግባር የሚገልጹት ምላሽ ነው፡፡ በሁለቱም ሰዎች ልናገኝ የምንችለው ምላሽ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለቋንቋው ያለን አመለካከት ነፀብራቅ ነው፡፡ ይህም ለአንድ ቋንቋ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ Gardner (1985፡41) ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ በማጠናከር የአመለካከት ምንጮችን በሁለት ክፍሎች መድበው ይመለከቷቸዋል፡፡

እነሱም አጠቃላይ ዝርዝር፣ ማህበራዊና ትምህርታዊ በማለት ነው፡፡ ዝርዝር ብለው የሚመለከቷቸው ተማሪው ስለሚማረው ቋንቋና ስለ ትምህርቱ ያለውን አመለካከት ሲሆን አጠቃላይ የሚሏቸው ደግሞ ስለ ቋንቋ ትምህርትና ስለ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለውን አመለካከት ይይዛል ይላሉ፡፡ Gardner በመቀጠልም ትምህርታዊ በሚሏቸው ውስጥ ተማሪው ለመምህሩ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያ ስልቱና ሁኔታው፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎችና በአጠቃላይ ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር በሚገናኙ ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከት ያጠቃልሏቸዋል፡፡ በማህበራዊ ስር ደግሞ ተማሪው ስለ 2ኛ ቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ፣ ስለ ባህላቸው፣ ስለ ቋንቋቸውና ስለ ሌሎች ከትምህርት ውጪ የሆኑ ጉዳዮችን ያካትታቸዋል ብለዋል፡፡

በ Oppenheim (1984) አገላለፅ አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎት፣ ምኞትና ግምት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በባህሪው ውስብስብ፣ ረቂቅና በአይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ነገር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም በቀላሉ የማይታወቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ሀሳብ ያለው (2001 ፣ 62) ሲያጠናክሩት፡-

> *"አመለካከት ረቂቅ የሆነ በገሀድ በአይናችን ልናየው፣ በጆሯችን ልንሰማው፣ በእጃችን ልንዳስሰው የማንችል ነገር ግን መኖሩን የምናውቀውና በተለያዩ መንገዶችን እንደሚከሰት የምንረዳው፤ ስውር ወይም ድብቅ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ መነሳሳት፣ ፈጠራ፣ እውቀት፣ ፍላጎ፣ ጭንቀት ወዘተ የመሳሰሉት እንዳሉ እናውቃለን፡፡ እነዚህም ነገሮች በባህሪያችን ተፅእኖ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በዕለት ተዕለት ክንዋኔዎችም ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡"*

በአጠቃላይ Mckay and Hom Berger (1996፡3-4) እንደገለፁት በግለሰብ ደረጃ በተማሪዎች ላይ ባለ የቋንቋ አተያይ ቋንቋውን ለመማር ባለው ማህበራዊ አውድና በቋንቋ ትምህርቱ ስኬታማነት መካከል ያለውን ግንኙነት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ፣ መልሱ ከባድና በቀላሉ ሊመለስ የሚይችል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ለአንድ የቋንቋ ትምህርት ስኬታማነት እጅግ በጣም ብዙ ተላውጦዎች ቢኖሩም ከነዚህ ተላውጦዎች መካከል በቋንቋው ላይ የሚታይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ አመለካከት አንዱና ዋነኛው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በአንድ ቋንቋ ላይ ቀና አተያይ ካለ የቋንቋ ትምህርቱ ወይም ለመዳው ስኬታማ መሆን እንደሚችል ሲታመን በቋንቋው ላይ ያለው አተያይ አሉታዊ ከሆነ ግን የቋንቋ ትምህርቱ ስኬታማ ለመሆን ያለው እድል የመነመነ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

### 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

እጥኘው በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እየሰራ ያለ ሲሆን ልምድ ካላቸው መምህራን ማረጋገጥ እንደቻለችው ታላሚው ቋንቋ ለረጅም ጊዜ እየተሰጠ የቆየ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን አጥኘው በመማር ማስተማሩ ሂደት እና በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል  ሁኔታ እና ውጤት ላይ ችግር ያጋጠመ በመሆኑ፣ ችግሩ ከምን የመነጨ እንደሆነ ለማወቅ እንዲሁም ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከግምት ባለፈ በውል ያልታወቀ ስለሆነ ታላሚውን ቋንቋ በማስተማር ሂደት ውጤታማ ለመሆን አስቀድሞ የተማሪዎችን አመለካከት ማወቁ የተሻለ ነው ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ ያሳደረውን ጫና ሲፈትሽ  የትምህርት አቀባበላቸውም ሆነ  ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑ ይህንን ጥናት እንዲያደርግ አነሳስቶታል፡፡

### 1.4. የጥናቱ ዓላማ

በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤት የሚማሩ እና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ -ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት እንዲሁም አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ በመፈተሽ አመለካከታቸውን ከአሉታዊ ወደ አውንታዊ መቀየር እና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማጅረግ ነው ዝር ዓላማዎቹ፡-

- አመለካከት ምንድነው የሚለውን ጥያቄ  መመለስ፣
- ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ወይስ አሉታዊ የሚለውን መለየት፣
- በተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ ተጽእኖ አድራጊ ተላውጦዎችን ለይቶ ማወቅ፣
- አመለካከታቸው ውጤታቸው ላይ ያሳደረውን ጫና ለይቶ ማወቅ እና ውጤታቸውን ማሻሻል ነው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

- የዚህ ጥናት ጠቀሜታ በፊዴ ትምህርት ቤት የሚገኙ እና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አውንታዊ በመቀየር የተሻለውጤት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚወሰነው በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በፊዴ ሁለተኛ ድረጃ የሚማሩ እና በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠንኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ  መዳሰስና ለነዚህ ችግሮች መፍችሄ መፈለግ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሆኑ ጉዳዮችና ሌሎች በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ክፍሎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሥነት

ይህ ጥናት በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ እና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እና አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚዳስስ ሲሆን ለመረጃ ማሰባሰቢያነት የተጠቀመውም የጽሑፍ መጠይቅን እና ፈተናን ነው፡፡ በወረቀት ውድነት እና ፀሐፊዎች በሚጠይቁት ከፍተኛ ዋጋ ምክንያት ሌሎችን የመርጃ ማሰባሰቢያ ያለመጠቀሙ የጥናቱን ውስንነት ያሳያል፡፡

## 1.8 የጥናቱ ጥያቄዎች

### 1.8.1 የጥናቱ መሪ ጥያቄ

በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ እና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት እና የዉጤት ተዛምዶ ምን ይመስላል?

### 1.8.2 የጥናቱ ንዑሣን ጥያቄዎች

በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ እና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

፡ አወንታዊ ነው? ወይስ አሉታዊ ?

፡አመለካከታቸው ከውጤታቸው ጋር ያለው ጫና ምን ይመስላል ?

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1. የአመለካከት ምንነት

እንደ Gardner (1985:8) አገላለፅ አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት እምነትና ግምት ወዘተ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በባህሪው ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ፣ ረቂቅና ድብቅም ነው፡፡ ከዳበረ ልምድና ባህሪይም ጋር ተወሳስቦ የሚገኝና ድብቅም በመሆኑ ስለ አንድ ጉዳይ የሚኖር የሰዎች አመለካከት  አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሊገለፅ ሲችል በሌላ ጊዜ ደግሞ ይደበቃል፡፡ ይሁን እንጂ በቀላሉ ከጉዳዩ ጋር ሊገናኝ ከሚችል ሁኔታ ጋር ተገናኝቶ ሲመረመር ወይም እንዲወጣ የሚገፋፋውና የሚያነሳሳው አጋጣሚ ሲገኝ በቃል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ወይም በገሃድ ሊታይ በሚችል ድርጊትና የባህርይ ግልጠት ሊታወቅ ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀው  ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አመለካከት ውስጣዊ ስሜት ሆኖ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና በተለያዩ አጋጣሚዎች ወይም ክስተቶች በሰዎች ባህርይ ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ኃይሉን መግለፅ የሚችል መሆኑንና ይህም ስሜት በተመሳሳይ መልኩ ከጉዳዩ ጋር ሲገናኝ የባህሪ ለውጥ የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አመለካከት የሠዎች ውስጣዊ ስሜት ሲሆን አንድ ቀስቃሽ ወይም አነሳሽ የሆነ ምክንያት ተከትለው ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው ጥቅል ስሜት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመለካከት የምንለው ሰዎች ስለ ራሳቸው የሚሉትን ወይም የሚገልፁትን ሳይሆን ለአንድ አነሳሽ ጉዳይ የሚሰጡትን ምላሽ በማጤን ራሳችንን የምንመለከትበት  ሁኔታ መሆኑን ነው፡፡

Fasold (1984:147) አመለካከትን እንደገለፁት "አመለካከት ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ምክንያቶች ለአንድ ነገር የሚኖራቸው አመለካከት ወይም ስሜት ነው፡፡ ሰዎች ከማህበራዊና ስነልቦናዊ ቀስቃሽ ሁኔታዎች ተነስተው የሚሰጡት ወይም በተግባር የሚገልፁት ምላሽ ነው፡፡ ይህ ምላሽም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡"

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው የሰዎች አመለካከት ከማህበራዊ ወይም ስነልቦናዊ ክስተቶች እንደሚመነጨ ወይም እንደሚነሱና ይህም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንደሚሆን ነው፡፡

ይህ አውንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት ሰወቹ በዚያ ዙሪያ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ጋርም ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት አለው። ይህም ማለት ሰዎች በነገሮች ላይ እውንታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ውጤቱም ያማረ ይሆናል።አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ደግሞ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ።

በMcGroatty (1996:5) አገላለፅ አመለካከት አዕምሯዊና ስሜት ነክ ነው። ይህም በመሆኑ ስለ አንድ ነገር ያለንን እምነትና ስሜታዊ ባህርይ አካቶ ይይዛል። በተጨማሪም አመለካከት ሰፋ ባለ መልኩ የሰዎችን ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ለማስተዋልና ባህሪያቸውንም ለመገምገም ያስችላል። ስለዚህ አመለካከት ሰዎች በአንድ ነገር ላይ ካላቸው እምነትና በዚያ ነገር ከሚሰጡት ግምት ወይም ቦታ ጋር ይገኛል ለማለት ያስደፍራል። የሚያስመዘግቡትም ውጤት ከዚሁ ጋር ይያያዛል ።

የምሁራን ሀሳብ እንደሚያመለክተው በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ያለ ስሜት ሆኖ ለተለያዩ ነገሮች ያለንን ግምትና ስሜት የሚያሳይ፣ እንዲሁም ስነልቦናዊ የሆኑ ክስተቶችን በማስተዋል ለእነዚያ ነገሮች ያለንን ስሜት መገመት የሚያስችል ሁነት እንደሆነ ነው።

Mechrens & Lehmann (1984:238) እንደገለፁት አመለካከት ሰዎች በአንድ ነገር ላይ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸውና ምን አይነት አኳኋን እንደሚኖራቸው የሚያመለክት ነው። የተለያዩ ሰዎች በአንድ ነገር ወይም ሁነት አንድ አይነት አተያይ ላይኖራቸው ይችላል። የሚያስመዘግቡትም ውጤት የተለያየ ነው። ምክንያቱም ባህሪያቸው የተለያየ ነውና በመሆኑም አመለካከት አንድ ሰው ለአንድ ነገር ወይም ሁኔታ ላይ ባለው አተያይ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አመለካከት በተለያዩ ነገሮች ላይ የሚኖረንን ስሜት የሚመለከት ሆኖ ስሜታችንም እንደየሁኔታዎች ልዩነት እንዳለው ያሳያል። ምክንያቱም የሁነቶቹ ባህሪይ የተለያየ ስለሆነ አተያያችንም የተለያየ ይሆናል።

በMorgan (1986) አገላለፅ አመለካከትን ስንገልፅ በግለሰቦች ገለፃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በአንድ ነገር የሚሰጡትን ግምገማ የሚወክል ነው። በመቀጠልም ማንኛውም ግምገማ ስሜት የሚቀሰቅስ ነገር ለአንድ ሁኔታ ወይም ነገር አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል። ከዚሁ ጋር አያይዘው ለአንድ ነገር የሚኖረን ግምት የመውደድ የመጥላት፣ የመደገፍ የመንቀፍ፣

የመስማማትና ያለ መስማማት ሁነቶች አዎንታዊና አሉታዊ በሆኑ ምላሾች ይገለፃሉ ብለዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው በእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ፍቺ ወይ ትርጉም ሆኖ አንድ ሰው ለአንድ ሁነት ወይም ነገር የሚሰጠውን የስሜት ቅርበት የሚያመለክት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ስሜትም የመራቅ የመቅረብ ቦታ የመስጠትና ያመለስጠት አዎንታዊና አሉታዊ አቀራረቦችን የሚመለከት ነው፡፡ የምናስመዘግበው ውጤትም ከዚሁ ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ነው፡፡ይህም ማለት በቀረብናቸው ወይም ቦታ በሰጠናቸው ጉዳዮች ላይ ጥሩ ውጤት የምናስመዘግብ ሲሆን በተቃራኒው ባልቀረብናቸውና ቦታ ባልሰጠናቸው ጉዳዮች ላይ ዝቅተኛ ነጥብ ማስመዝገብ በሰው ልጅ ላይ የሚታዩ ባህርያት ናቸው፡፡

Kuppuswamy (1984) እና Aggarwal (1998) እንደገለፁት አመለካከት ከውልደት በኋላ በእድገት ሂደት የምናዳብረው የስብዕና ክፍል ነው፡፡ ይኸውም ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችንና ክስተቶችን ወዘተ የመውደድ፣ የመጥላት፣ የመደገፍ የመንቀፍ፣ የመቅረብ የመራቅ ዝንባሌንና ስሜትን የሚያመለክት የስብዕና ዘርፍ ነው፡፡ እነዚህ ባህሪያት ደግሞ በውስጣችን ሊጠነሰሱ የሚችሉት በተለይ ራሳችንንና አካባቢያችንን ለይተን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ይነሳና በሂደት የምናዳብረው ሂደታዊ የሆነ የባህሪ ለውጥ እንደሆነ ምሁራኑ ይገልፃሉ፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንገነዘበው አመለካከት አብሮን የሚወለድ ሳይሆን ከተወለድን በኋላም ክፉና ደጉን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የሚከሰትና እንደ አስተሳሰባችን ብስለትና ጥንካሬ በእድገት ሂደታችንን አብሮ የሚያድግ እንደሆነም ያሳያል፡፡ ይህ የማንነታችን ክፍል የሆነው አመላከከትም የሚገልፅበት ለአንድ ነገር የሚኖረን የስሜት ርቀትና ቅርበት መሆኑን ነው፡፡

Gardner (2006) Malim እና Birtch (1998) እንደገለፁት አመለካከት የተደራጀና ተከታታይነት ያለው ሰዎችን፣ ቡድኖችንና ማህበራዊ ጉዳዮችን በአጠቃላይ በአካባቢው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ አዕምሯዊ ስሜታዊና ባህሪያዊ ክስተት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም አመለካከት በአካባቢው በሚከናወኑ ማህበራዊ አውድ ላይ የተመሰረተና የሰዎች አዕምሯዊ ስሜት እንደሆነ ያስረዳል፡፡

Rosenberg & Howland (1980) አመለካከት የሠው ልጅ ከተፈጥሮ ክስተቶችና ከራሱ ህሊና ጋር ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜ በምናቡ አንድ ክስተት ሊከሰትበት ይችላል፡፡ በስሜቱ

አማካኝነት ስለሚያስበው ወይም ተራክቦ ስለሚያደርግበት ርዕሰ ጉዳይ አንድ እምነት ወይም ስሜት በልቡ ያድራል፡፡ እነዚህ የፈጠራቸው እምነቶችና ስሜቶች አንድን ተግባር ለማከናወን ያስችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ ተግባርን ለማከናወን የሚደርስ ውሳኔ ወይም ውጤት ይፈጥራሉ፡፡ ይህ ውሳኔ ወይም ውጤት ጥሩ ወይም መጥፎ ስሜትን የመፍጠር ሂደት አመለካከት ይባላል፡፡

አመለካከት በሰዎች ልብ ላይ የሚያድር አንዳች ስሜት ሆኖ ነገሮችን ለማከናወንና ላለማከናወን የሚያስችልና እነዚያን ነገሮች እንድናከናውን ወይም እንዳናከናውን በልባችን ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድርም እንደሆነ ነው፡፡ ይህ በልባችን ውስጥ የሚያድረው ተጽዕኖ ደግሞ ከምናስመዘግበው ውጤት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው፡፡ ያደረብን ተጽዕኖ አወንታዊ ከሆነ ጥሩ ውጤት አሉታዊ ከሆነ ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገባችን አይቅልሬ ነው ፡፡

## 2.2. አመለካከትን የማጥናት አስፈላጊነት

አዎንታዊ የሆነ አመለካከት በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቦታ፣ በማህበራዊ መስክ በኢኮኖሚያዊ መስክ በፖለቲካዊ መስክ ሳይቀር ውጤታማ ተግባርን ለማከናወን የተሻለ ውጤትም ለማስመዝገብ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም በሁሉም መስክ ያለውን የአመለካከት ሁኔታን ማጥናት ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በSkinner (1985)፣ Spolsky (1998)፣ Harmer (1991) እና Brown (2007) አገላለፅ በአመለካከት ላይ የሚደረግ ጥናት በማህበራዊ ስነ አዕምሮ ግንባታ የመጀመሪያው የመሰረት ድንጋይ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ አመለካከት ከማህበራዊና ከስነ አዕምሯዊ ሁኔታዎች የሚመጣ ስለሆነ በትምህርቱና በሌሎች የተግባር መስኮች ዙሪያ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ አመለካከት የሚገኝበትን ሁኔታና አዎንታዊና አሉታዊ መንስኤዎቹን ለማወቅ በጥናትና ምርምር በማወቅ በመማር ማስተማር ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት አስፈላጊነቱን ያጎላቸዋል፡፡ አዎንታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ የሚሰጠውን ትምህርት ለመማር አዎንታዊ የሆነ ስሜት  እንደሚያሳድር ሁሉ በተቃራኒው አሉታዊ አመለካከት ያለው ደግሞ አሉታዊ ተነሳሽነትና ፍላጎት እንደሚኖረው ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን ማንነት ለማወቅ የተማሪዎቹን ታሪክ ማወቁ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተማሪዎች ታሪክ ሲባል እድሜ፣ ፆታ፣ የዕውቀት ዳር፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዳር፣ የስራ ሁኔታ፣ ፍላጎትና እምነት ስነልቦናዊ ሁኔታ ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ዙሪያ ያለውን እውቀት ማጥናት ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤትም በመነሳት ምን አይነት የማስተማሪያ

መሳሪያ መምረጥ እንደሚያስፈልግ ለመወሰንና አዘጋጅቶ ለማስተማር ይረዳል፡፡ በዚህ መንገድ የተማሪዎቹን ዳር ማወቁ የተማሪዎቹን ትክክለኛ የሆነ ፍላጎታቸውን ለመረዳትና በዙሪያው ለሚስተዋሉ ችግሮች ማስተካከያ ለመስጠት ይረዳል፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው አመለካከት ከማህበራዊና ስነ አዕምሯዊ ጉዳዮች የሚመጣ በመሆኑ በተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ወይም የጥናት መስኮች ዙሪያ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ስለሆነ ሊጠና የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በGardner (2006) አገላለፅ ከመማር ማስተማር አንፃር ለአመለካከት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱንም ሲገልጹ ተማሪው ለትምህርቱ ካለው ንሺና በትምህርቱ ከሚያስመዘግበው ውጤት ጋር በማያያዝ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ተማሪው አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለትምህርቱ የመማር ፍላጎት ወይም ንሺ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ለትምህርቱ ንሺ ያለው ተማሪ ደግሞ ውጤታማ ስለሚሆን አመለካከትን ማጥናት አስፈላጊ ከሚያደርጉ ነጥቦች ውስጥ አንዱ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል Krashen (2009) እና Gardner (1985) እንደገለፁት "ለምናከናውነው ተግባር አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ከሌለ የሚመዘገበው ውጤት ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለስራ የሚኖረው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን ስለሚያደርገው ነው" ይላሉ፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው ለምናከናውነው ተግባርና ለምናስመዘግበው ውጤት መሰረቱ አመለካከት እንደሆነና ይህም በጎና በጎ ያልሆነ አመለካከት ያለ ሲሆንለት አመለካከት ለጥሩ ተነሳስኦትና ውጤት እንደሚያበቃ ያስገነዝበናል፡፡

## 2.3. አመለካከት በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

Gardner (1985) እና Masgort & Gardner (2003) እንደገለፁት "ቋንቋን ለመማር ጥሩ የሆነ ግንዛቤና ስሜት ከሌለን በትምህርት ሂደት ላይ መልካም ፍላጎት አይኖርም፤ ፍላጎት ከሌለ ደግሞ ንሺ አይኖርም፡፡ ተማሪው ለሚማረው የ2ኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከትና ተነሳሽነት ከሌለው ትምህርቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመከታተል አዳጋች ስለሚሆን ውጤታማ መሆኑ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የተማሪን ፍላጎትና ማንነት ማወቁ ተማሪው ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖረው ለማድረግና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲባል

አመለካከትን ማጥናት ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በተዋጣለት መንገድ በመስጠትና ለማከናወን ከመረዳቱም በተጨማሪ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ለመጠቀም ሲባል የተማሪዎችን አመለካከት ማጥናቱ ወሳኝና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸውን የአመለካከት ደረጃ ማጥናት የሚያስፈልግበት ምክንያት ለተለያዩ ተማሪዎች እንደየ ልዩነታቸውና ልዩ ባህሪያቸው አስፈላጊ እገዛ ለማድረግ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማስቻል ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

Celce- Murcia (1991) እንደገለጹት ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ከሌለው ለትምህርቱ ንሺ ስለማይኖር ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩበት አውድ በአመለካከታቸው ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የተማሪውን ቋንቋ የሚማርበት አውድ ሲባል የማስተማሪያ ዘዴውን፣ የመረጃ መሳሪያውን፣ የመምህሩ አቀራረብ፣ ትምህርቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑ ተማሪው ለትምህርቱ ጥሩ የሆነ እይታ ኖሮት የሚከታተልበትን መንገድ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ የትምህርት አውድ በተማሪው አመለካከት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ካለ በ2ኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ውጤታማ ሊያድርግ እንደሚችልና አሉታዊ ከሆነ ደግሞ በትምህርቱ ላይ ጫና እንደሚያሳድር ያስረዳናል፡፡

በተቃራኒው ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች አሉታዊ አመለካከት ያለው ከሆነ ቋንቋውን የመማር ፍላጎት እንዳይኖረው ከማድረግም አልፎ ትምህርቱ በሚሰጥበት ሰዓትም ደስተኛ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የ2ኛ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪው የሚማረው እየተሰጠ የሚገኘውን የቋንቋ ክህሎትና እውቀትን ብቻ ሳይሆን የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልም ጭምር ነው ይላሉ፡፡

ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ወቅት የሚኖረን አሉታዊ አመለካከት በመማሩ ሂደት ላይ እንዲሁም በምናስምዘግበው ውጤት ላይ አሉታዊ የሆነ ተፅዕኖ ስለሚያሳድርብን ቋንቋውና ተናጋሪ ማህበረሰቦችን የመራቅና የመማር ተነሳሽነት ዝቅተኛ የመሆን ክስተቶችን እንደሚፈጥሩ ያሳየናል፡፡

Lightbown (2011) እንደ አጠቃላይ ሲታይ ማህበራዊ ምክንያቶች በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ ንሺና በትምህርቱ ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለው አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ያሳያል፡፡ ይህ ማለት ተማሪው በቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ካለው እንደ አፈ ፊት ተማሪው ለመናገር ጥረት ስለሚያደርግ በድፍረት መናገር ይችላል፡፡ ጥሩውጤትም ያስመዘግባል፡፡ ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት ለመፍጠር ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ያሳድራል ብለዋል፡፡

የምሁራኑ ሀሳብ እንደሚያስገነዝበው የቋንቋው ተማሪ ለታላሚ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለው ቅርርቦሽ ወይም አዎንታዊ አመለካከት ከመማር ማስተማር ሂደቱም ሆነ በቋንቋው ለመዳማ ውጤታማነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ያስረዳል፡፡

## 2.4. ለአመለካከት መፈጠርና መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች

አመለካከት ከበህርይ ለውጥ ውስጥ አንዱ ሲሆን  ለውጡም ቀስ በቀስ እየተለወጠና እየተፈጠረ የሚሄድ ነው፡፡ የሠው ልጅን የእድገት  ሂደት መሰረት በማድረግ የሚፈጠር አለበለዚያም በተወሰነ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚከሰት ቀጣይነት ያለው ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰቱ ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር የሚመጣ ነው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አመለካከት ከአባቢያዊ ሁኔታን፣ የእድሜ ክልልን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን መሠረት አድርጎ ሊፈጠር የሚችል የባህሪ ለውጥ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ምሁራን ስለ አመለካከት መለወጥ የሰጡትን ሀሳብ እንደሚከተለው እንመልከት፡-

Malim and Birtch (1998) አመለካከት ከባህርይ ለውጥ ውስጥ አንዱ ሲሆን ለውጡም ቀስ በቀስ እየተለወጠና እየተፈጠረ የሚሄድ ነው፡፡ የሰው ልጅን እድገት መሰረት በማድረግ የሚፈጠር አለበለዚያም በተወሰነ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚከሰት፣ ቀጣይነት ያለው ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰቱ ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር የሚመጣ ነው፡፡ አመለካከት አካባቢያዊ ሁኔታን፣ የዕድሜ ክልልን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን መሰረት አድርጎ ሊፈጠር የሚችል የባህርይ ለውጥ ነው፡፡ ለአመለካከት መፈጠር መነሻ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም በተለይ እስከ ወጣትነት እድሜ ላሉት ልጆች፣ ወላጆች፣ ማህበረሰቦች፣ ባህል፣ የእድሜ እኩዮችና መምህራን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው ከተወለዱበት አንስቶ

ራሳቸውን እስከሚችሉበት ድረስ በአነጋገራቸው፣ በፍቅርና ጥላቻቸው፣ በእምነታቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በአመጋገባቸውና ማህበራዊ ተራክቦዎች ከተለያየ የማህበረሰቡ አካላት ጋር ያላቸውን ተግባቦት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የበዓል አከባበር የሚከተሏቸው ስነ ስርዓቶችን፣ ታሪክ፣ የአስተሳሰብ ስሜቶችና ክንውኖች ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በዚህም አነጋገርን የመጥላትና የመውደድ ዝንባሌን ከቢጤዎች መኮረጅ የተለመዱና የወጣት ሰዎች ባህሪያት ናቸው፡፡ ለመዝናናትም ሆነ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ከእኩዮቻቸው ጋር በመሆን ነው፡፡ አብሮነት ደግሞ የፍላጎት፣ የእምነትና አመለካከት ወዘተ መጋራትን እንደሚያስከትል መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል እንደሚችል ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ ምሁራን አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Russell (1989) አመለካከት ከከፍተኛ አዎንታዊነት ወደ አሉታዊነት፣ ከከፍተኛ አሉታዊነት ወደ አዎንታዊነት ሊለወጥ መቻሉን አስፍረዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም አንዴ የዳበረን አመለካከት ለመለወጥ አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜም አለ፡፡ምክንያቱም አንደኛው አመለካከታችንን ወይም እምነታችንን ሊለውጡ የሚችሉ ጉዳዮችን ካለማስተናገድ የሚመጣ ነው፡፡ ሌላው ወቅታዊ ወይም ከዘመናዊነት አተያይ እና ትርጓሜ ጋር በማያያዝ በሚመጣ የግትርነት አስተሳሰብ ምክንያት የሚመጣ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ከቀረበው ሀሳብ በመነሳት ማጠቃለል የሚቻለው አመለካከት አንዱ የባህርይ ክፍል ሲሆን ይህ የባህሪ ክፍል በተለያዩ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ወይም ተፅዕኖ ፈጣሪነት ምክንያት መለወጥ መቻሉን ሲያመለክት ለውጡም ከከፍተኛ አዎንታዊነት ወደ አሉታዊነት ወይም ከከፍተኛ አሉታዊነት ወደ አወንታዊነት አወንታዊነት እንደሚሆን ነው፡፡ ስለዚህ ለአመለካከት መለወጥና መፈጠር በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ሰው የሚገኝበት ማህበራዊ አውድ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ኢኮኖሚያዊ ትምህርታዊና አካባቢያዊ ለውጦችን መሰረት ያደረገ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

Fasold (1984) እንደሚገልፁት አንድ አድማጭ ለተናጋሪው የሚሰጠው ምላሽ ተናጋሪው ስለሚናገረው ቋንቋ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲኖረው እንደሚያደርግ ይገልፃሉ፡፡ አንድ ተናጋሪ ለሚናገረው ቋንቋ የሚኖረውን አመለካከት በሚሰጠው ምላሽና አድማጩ ከንግግሩ በመነሳት ለተናጋሪው በሚሰጠው ደረጃ ይወሰናል፡፡ የአድማጭ ምላሽ ገንቢ ወይም አፍራሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ተናጋሪው ለቋንቋው የሚኖረውን አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊያደርገው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ሌላው የአመለካከት ምንጭ የሚባለው

የቋንቋዎች ስነልቦናዊ ቅርርቦሽ ነው፡፡ ሁለት ቋንቋዎች በዝምድና፣ በውሰት ወይም በአጋጣሚ ተመሳሳይ የሆነ ስነልቦናዊ ቅርፅ ሊይዙ ይችላሉ፡፡ በተለይ ቋንቋዎች ዝምድና ካላቸው እንዲህ አይነቱ ቅርርቦሽ ከፍተኛ እንደሚሆን ይገልፃሉ፡፡ በሁለቱም ቋንቋዎች ተመሳስሎሽ አለ ሲባል በድምፅ በምዕላድ በቃልና በአገባብ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ በሌላው ቋንቋ የሚተላለፉ መልዕክቶችን በቀላሉ የመረዳት አጋጣሚ ስለሚፈጠርለት ለሚማረው 2ኛ ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ሊፈጠር ይችላል ጥሩ ውጤትም ያስመዘግባል ብለዋል፡፡

Brown (1994:162) እንደገለጹት ሌላው የአመለካከት መሰረታዊ ምንጮች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው ንሺ (motivation) ነው፡፡ ንሺ አንድ ነገር ለመስራት ሰዎችን የሚገፋፋና የሚያነሳሳ ስሜት ነው፡፡ ንሺ በ2ኛ ቋንቋ የመማር ሂደት ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር የሚኖራቸው ውስጣዊ ፍላጎት የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተማሪዎች ንሺ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የንሺ ጠንካራ መሆን አለመሆን ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው ከጨረሱ በኋላ እንደርስበታለን ከሚሉት ግብ ጋር ተያያዥነት አለው ብለዋል፡፡

ይህ ማለት ተማሪዎች የ2ኛ ቋንቋ ትምህርትን ተምረው ውጤታማ ለመሆንና ከፈለጉት ለመድረስ የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው ያሳያል፡፡ ማለትም ከፍተኛ ወይም ጠንካራ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ውጤታማ ወይም ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ አመለካከትን ያዳብራሉ፤ ጥሩ ውጤትም ያስመዘግባሉ ማለት ነው፡፡

Gardner (1985:41) የተማሪዎችን የአመለካከት ምንጮች በሁለት ክፍሎች መድበው ይመለከቷቸዋል፡፡ እነዚህ አጠቃላይና ዝርዝር፣ ማህበራዊና ትምህርታዊ የሚሏቸው ናቸው፡፡ ዝርዝር ብለው የሚመለከቷቸው ተማሪው ስለሚማረው ቋንቋ ትምህርትና ስለ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለውን አመለካከት ይይዛል ይላሉ፡፡ በመቀጠልም ትምህርታዊ ከሚሏቸው ውስጥ ተማሪው ለመምህሩ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያ ስልቱና ሁኔታው፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎችና በአጠቃላይ ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር ከሚገናኙ ጉዳዮች ጋር ያለውን አመለካከት ያጠቃልላሉ፡፡ በማህበራዊ ስር ደግሞ ተማሪው ስለ 2ኛ ቋንቋ ተናጋሪው ማህበረሰብ፣ ስለ ባህላቸው፣ ቋንቋቸውና ስለ ሌሎች ከትምህርት ውጭ የሆኑ ጉዳዮችን ያካትታል ብለዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ትምህርታዊና ከትምህርት ውጭ የሆኑ ማህበራዊ ጉዳዮች የአመለካከት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉና በተማሪው አመለካከትም ሆነ ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

## 2.5. ቋንቋንና የቋንቋ ትምህርትን አስመልክቶ በተማሪው አመለካከት እና ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

ለአመለካከትና መለወጥ መነሻ የሚሆኑ ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ በተለያዩ የምሁራን ሀሳቦች ላይ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ስለዚህ በጎ አመለካከትን ማዳበርና እንዲጎላ ጥረት ማድረግ የመማር ማስተማር ትልቁ አላማ መሆኑ ያስማማል፡፡ ነገር ግን የተፈለገውን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉና አሉታዊ የሆነ አመለካከት እንዲፈጠርና በአዎንታዊ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ክስተቶች አሉ፡፡ በመሆኑም መንስኤ የሚሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለይቶ ባለማወቅ የሚከሰት ነው፡፡ ለዚህ መፍትሄ ለመሻትም በአንድ የትምህርት አይነት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ነጥቦችን አስመልክቶ መረጃ በማሰባሰብና በመተንተን ችግሮችን ለይቶ ማወቅና ማስተካከያ መስጠት ከተቻለ የመማር ማስተማር ተግባሩን ውጤታማ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠልም ተማሪዎች በሚማሯቸው የትምህርት አይነቶች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ተፅዕኖ አሳዳሪ ክስተቶችን በምሁራኑ ሀሳብ በማስደገፍ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### 2.5.1.ጓደኛ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ

በHurlock (1996), እና Harmer (1983) አገላለፅ "ከተማሪዎች አመለካከት ላይ አሉታዊ ድባብ ከሚፈጥሩ ሁኔታዎች ውስጥ የእኩዮች አመለካከት ዋናው ነው" ይላሉ፡፡ ምሁራኑ እንደገለፁት ጓደኞች ወይም እኩዮች በሚኖረን አመለካከት ላይ ከፍተኛ የሚሆነውን ወይም ሰፊ ሽፋን ያለውን ተፅዕኖ ፈጣሪ ናቸው፡፡ "ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን ልንገርህ" እንዲሉ አበው ልጆች ወይም ተማሪዎች አብረውት የሚውሉትን ይመስላሉ፡፡ በተለይ በ2ኛ ቋንቋ ሂደት ውስጥ የተማሪው ጓደኛ በቋንቋው ተማሪ ላይ ለውጥ የሚያሳድር አካል ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ የእኩዮችን አመለካከት ተመሳሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ጓደኞቹ ከወደዱት ይወደዋል ከጠሉት ደግሞ ይጠለዋል፡፡

የተማሪው እኩዮች በ2ኛ ቋንቋ መማር ሂደት ታላሚውን ቋንቋ በሚማረው ተማሪ ላይ ተፅዕኖ ያደርጉበታል፡፡ Harmer (1991:436) ይህን ሀሳብ በማጠናከር እንደገለፁት ተማሪው በትምህርት ቤትና በአካባቢው ብዙውን ጊዜውን የሚያጠፋው ከእድሜ እኩዮች ጋር ነው፡፡ በዚህ አማካኝነት አብረውት የሚውሉት ተማሪዎች የሚወዱትን ነገር ይወዳል፤ የሚጠሉትን ነገርም አብሮ ይጠላል፡፡ በመሆኑም በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት የተማሪዎች ጓደኞች የቋንቋ ትምህርት የሚወዱ ከሆነ ተማሪውም ይወደዋል፤ የሚጠሉ ከሆነ ደግሞ እንዲሁ ይጠለዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ሁሉም ሰዎች ከመሰሎቻቸው ጋር ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ ማለትም ህፃናት ከህፃናት ጋር፣ ወጣቶች ከወጣቶች ጋር፣ ጎልማሶች ከጎልማሶች እንዲሁም አዛውንቶች ከአዛውንት ጋር ጓደኝነትን ይመሰርታሉ፡፡ በዚህም በሀሳብ የሚግባቡ የሚደማመጡና የሚረዳዱ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችም ጓደኝነት ከሚመሰርቱት እኩዮቻቸው ጋር በሀሳብ ተመሳስሎ ስላለና ስለሚግባቡ በአዎንታዊነትም ይሁን በአሉታዊነት ጓደኛ ወይም እኩዮች ተፅዕኖ ፈጣሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እንደ Harmer (1983) እና Hurlock (1996) አገላለፅ ወጣትነት እድሜ ተማሪዎች ከየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል በበለጠ በእኩዮቻቸው በጓደኞቻቸው ፍላጎት ይመራሉ፡፡ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ከወላጆቻቸው በበለጠ በእኩዮቻቸው ሀሳብና ምርጫ የመመራት ሁኔታ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ የሚረብሹ፣ የቤት ስራ የማይሰሩ፣ የማያጠኑ ከሆነ የእኩዮቻቸውን ዝንባሌ፣ ስሜትና አድራጎት ሊጋሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሰፊ ነው ይላሉ፡

ምሁራኑ እንደገለፁት በእኩዮቻቸው ምርጫና ዝንባሌ የመሳብ ሁኔታዎች ተዘውትረው የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ማንበብ የሚዘወትር ጓደኛ ያለውን ተማሪ ብንወስድ እሱም አንባቢ የማይሆንበትና በወሬው መካከል ስለ ንባብ ሊያነሳ ይስተዋላል፡፡ እንዲሁም ስለ ፊልም የሚያወራ ጓደኛ ያለውም እንዲሁ በተመሳሳይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የቅርብ ጓደኛቸውን ስለሚመስሉ ባላቸው የቋንቋ ትምህርት አመለካከት ብሎም በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩባቸው ይችላሉ፡፡

የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ቋንቋውን በደንብ ለመናገር ለመማር የቤተሰብ አመለካከት ወይም ለቋንቋው ያለው አተያይ ከፍተኛ ሚና እንዳለውና በተማሪው የቋንቋ ውጼታ ላይ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ጥናቶች አመልክተዋል፡፡ ይህም ወላጆች ስለ ትምህርቱ ያለውን ግንዛቤ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል፡፡ ትምህርቱ በማህበራዊ ህይወቱ ላይ ያለው ሚና ያላቸው

ግንዛቤ ዝቅተኛ ከሆነ፣ የሀገሪቱ ህግ ስለሚያስገድዳቸው ብቻ ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት የመላክ ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ይህ ደግሞ በልጆች ላይ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት እንዲዳብር የሚረዳ አይደለም፡፡ በዚህ ዙሪያ የተሰጡ የምሁራኑን ሀሳብ እንመልከት፡፡

እንደ McGroatty (1996:18-19) አገላለፅ በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች ለአንድ ቋንቋ የሚኖራቸው አመለካከት ባላቸው ግላዊ ተሞክሮና ታሪክ እንዲሁም በትምህርቱ አውድ ውስጥ ይሆናል፡፡ በቋንቋ ክፍል አካባቢ የአፈ ፈት ተማሪዎች የበላይነት የሚንፀባረቅበት ከሆነ የ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጥሩ ነገር ላይሰማቸው ይችላል፡፡ ይህም የ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከአፍ ፈት እኩል ለቋንቋ ትምህርት በጎ የሆነ አመለካከት እንደማያዳብሩ ያመለክታል፡፡ ከወላጆች አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ወላጆች በቋንቋው አማካኝነት ውርደትና ሀፍረት ይደርሳባቸው ከነበረ ያንን ጭቆናና በደል በማሰብ ልጆቻቸው ቋንቋውን እንዲማሩ አይፈልጉም፡፡

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ወላጆች በልጆች ላይ ተነሳሽነት ከመፍጠር ይልቅ የቀደመና በጎ ያልሆነ ታሪካቸውን በማውሳት ልጆች የ2ኛ ቋንቋውን የሚማሩበት ጥሩ ወይም መልካም የሆነ አውድ ከመፍጠር ይልቅ ቋንቋውን እንዲጠሉና አሉታዊ የሆነ አመለካከት እንዲያዳብሩ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም አፍ ፈት ተማሪዎች እነሱ የተሻሉ እንደሆነ በሚያሳዩት ተፅዕኖ የ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን ይጠሉታል፡፡

በHarmer (1983:4) አገላለፅ ቤተሰብና ማህበረሰቡ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የተማሪዎች ወላጆች ወይም የአካባቢው ማህበረሰብ በሚያገኟቸው ድጋፍ ለሚማረው ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ይኖረዋል፡፡ በተቃራኒው የተማሪው ወላጆች ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ በጎ የሆነ አመለካከት የሌላቸው ከሆነ በተማሪው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩ ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖረው ውጤቱም ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡

Dubin & Olshtain (1986:13-15) እንደገለፁት ለትምህርት የዋለ ቋንቋ ከሆነ በቋንቋው ላይ የሚስተዋል ዝንባሌ አለ፡፡ ይኸውም ተተኳሪውን ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ወላጆቻቸው በታሪክ አጋጣሚ ለቋንቋው በተለያዩ አጋጣሚዎች አዎንታዊ አመለካከት ካላቸው ይህ ቋንቋ ለሚወክለው ማህበረሰብና ባህል ከፍተኛ ግምትና አድናቆት ሲኖራቸው የ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ከፍተኛ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ በአጠቃላይ አዎንታዊ የሆነ የማህበረሰቡ አመለካከት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ አመርቂ ውጤት ይገኛል፡፡ በአንፃሩ አሉታዊ የሆነ ብቻ

የማህበረሰቡ አመለካከት ካለ ከታሪክ፣ ከፖለቲካና ማህበራዊ ግጭት ጋር የተሳሰረ ችግር ይፈጥራል። ይህ በመሆኑ ዝንባሌው አሉታዊ ከሆነ ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳስኦት የቀነሰ ይሆናል፤ ወይም ጨረሶ ሊጠፋ ይችላል። በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በ2ኛ ቋንቋ ትምህርት ወላጆች ከፍተኛ ሚና ያላቸው እንደሆነ ያሳያል። ይህም ልጆች ከቤተሰብ ወይም ከወላጆች በተለያየ መንገድ በተረት፣ በታሪክ. በምሳሌያዊ አነጋገር የወረሷቸውን ነገሮች በትምህርታቸው ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት ለማዳበራቸው እንደ ምክንያት ይሆናሉ።

በአጠቃላይ ወላጆች፣ ማህበረሰብና የተማሪ ጓደኞች በ2ኛ ቋንቋ መማር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች መሆናቸውን ለመገንዘብ ይችላል። ይህም ማለት ወላጆች፣ ማህበረሰብና ጓደኞች ለታላሚው ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ካላቸው ተማሪውም አዎንታዊ አመለካከት ይኖረዋል።ጥሩ ውጤትም ያስመዘግባል ። በአንፃሩ ምላሻቸው አሉታዊ ከሆነ የተማሪዎችም አመለካካት አሉታዊ ይሆናል ውጤታቸውም ዝቅ ይላል ማለት ነው።

እንዲሁም 2ኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የቋንቋ ትምህርትን መማር ብቻ ሳይሆን የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ማንነት፣ በባህልና ወግ ልማድን መማርንም ይጨምራል። በመሆኑም የተማሪ ወላጆች ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ አይነተኛ ሚና ወይም አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል። ስለዚህ ወላጆች የ2ኛ ቋንቋን ተማሪ ታላሚውን ቋንቋ በአግባቡ እንደሚረውና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረው ወላጆችም ሆነ ማህበረሰቡና ጓደኞች አዎንታዊ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል።

## 2.5.2. ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች

Hakmann. (1995፣467) እንደገለፁት የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከተማሪዎቹ ባህላዊ ዳራና ተግባቦታዊ ስልት ተቃኝቶ ለትምህርት ቤቶች አዎንታዊ ምርጫ በመስጠት አለመግባባትን የሚቀንስ መሆን አለበት። በአንፃሩ ደግሞ የተማሪዎቹ በራስ የመተማመን መንፈስ የሚያበረታታና ለለውጥ የሚሰራ መሆን ያስፈልገዋል። እንዲሁም የሌላውን ባህል በተማሪዎች ላይ በመጫን ሳይሆን የተማሪዎቹን ባህል ወደ ክፍል ውስጥ በማምጣት ተማሪዎቹ ራሳቸውንና ሌሎቹንም እንዲያውቁ ማህበራዊ ተራክቦ እንዲለምዱና እውቀትን

እንዲያዳብሩ ማበረታታት ይገባል፡፡ የ2ኛ ቋንቋ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የሚሆነው የቋንቋ አጠቃቀም በማህበራዊ አውድ የሚወስን መሆኑ ነው፡፡ የቋንቋ ተማሪው ቋንቋውን የሚጠቀምባቸው ማህበራዊ አውዶች ላይ ካላወቀ በስተቀር ግጭት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ትምህርት ከባህል ጋር የጠበቀ ትስስር ስላለውና የ2ኛ ቋንቋ ተማሪው ባህልና ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ባህል ሊለያይ ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ ተማሪው የባህል ግጭት ይገጥመዋል፡፡ ይህም ተማሪው በሚማርበት ጊዜ ሊፈጠር የሚችል ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የምሁራን ሀሳብ ጠቅለል ሲደረግ ባህልና ፖለቲካ በ2ኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ከቋንቋነት ባህሪያቸው አንፃር ስንመረምራቸው ሁሉም ቋንቋዎች የተናጋሪ ማህበረሰቦችን ባህል፣ ወግ ልማድና የአኗኗር ዘይቤ ታሪክና ወዘተ ለመግለጽ ስለማይሳናቸውና የሌላ ቋንቋ እርዳታ ስለማይፈልጉ እኩል ናቸው፡፡ ሆኖም ከውስጣዊ ባህሪያቸው ውጭና በልዩ ልዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ምክንያት ከስነ ፅሁፍ ሀብት፣ ከተናጋሪ ብዛት ከስርጭት አንፃር ከተናጋሪያቸው ህብረተሰብ በቴክኖሎጂ የማደግ ሁኔታ ወዘተ አንድ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ የመበላለጥ ሁኔታ ሊያሳይ ይችላል፡፡ ቋንቋው ከሚነገርበት ማህበረሰብ፣ አካባቢና ባህል ስንወጣ አንድ ቋንቋ ከሌላው አያንስም፤ አይበልጥምም፡፡ በዚህም ይሁን በሌሎች፣ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የተለያዩ ማህበረሰቦች ወይም ግለሰቦች በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚከሰት አተያይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይስተዋላል፡፡

በCook (1991:472) አገላለፅ በ2ኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት በተማሪው ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች መካከል ባህላዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በፖለቲካው በኩል ያለው ተፅዕኖ የበታችነት ስሜት እንደሚፈጠርና የአንድነት አመለካከት እንዲንሸራሸር አንድ ወጥ የቋንቋ አጠቃቀም ፖሊሲ እንዳይኖር የአገር ውስጥ የተግባቦት ሂደት እንከን አልባ እንዲሆን እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል ብለዋል፡፡

የምሁራኑ ሀሳብ እንደሚገልፀው ፖለቲካዊ ጉዳዮች በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት የበታችነትና የበላይነት እንዲሰማቸውና አንድ ወጥ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም እንዳይኖር መደረጉ እንደ ተጽእኖ ይቆጠራል፡፡

## 2.5.3. የመምህሩ ስብዕናና የማስተማሪያ ዘዴው

በቋንቋ መማር ሂደት የሚከሰቱ ጉዳዮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከመምህሩ ወይም ከማስተማሪያ መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ መምህሩ በመጀመሪያ ደረጃ ሙያውን የሚያከብር መሆን አለበት፡፡ በውስጡ ጥላቻ ቢኖር እንኳ ተማሪዎቹ ስሜቱን እንዲያውቁ ማድረግ የለበትም፡፡ እንዲህ ማድረግ ካልቻለ ግን ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ይጠሉታል፡፡ ለመምህሩና ለቋንቋው ትምህርትም አሉታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቹ በመምህሩ ቀና አተያይ ካላቸው ለትምህርቱም አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡

ይህን በተመለከተ Masgort & Gardner (2003) እንደገለጹት ተማሪው ቋንቋውን የሚማርበት አውድ ማለትም የማስተማሪያ ዘዴው፣ የመረጃ መሳሪያው፣ የመምህሩ አቀራረብ ትምህርቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆንና አለመሆን ተማሪው በትምህርቱ ጥሩ የሆነ እይታ እንዲኖረው የሚደረግበት እይታ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ የትምህርት አውድ በተማሪው አመለካከት እና ውጤት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ይላሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው መምህሩ ትምህርቱን የሚያቀርብበት የተለያዩ አውዶች ተማሪው ለትምህርቱ ያለውን ተነሳሽነት እንደሚወስኑና በታላሚው ቋንቋ ላይም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብሩ እንደሚችሉ ነው፡፡

Mckay and Hornberger (1996:13-15) እንደሚገልፁት ብዙ ጊዜ መምህራን ለራሳቸው የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ይህም ለምንድን ነው አንዳንድ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ሲበልጡ ሌሎቹ ግን በአብዛኛው ተመሳሳይ ዳራዊ እውቀት ላይ የሚገኙት? በምንድን ነው? ጥቂት ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይገባቸው ዘንድ ወይም ውጤታማ ለመሆን ሲጥሩ ጥቂቶቹ ደግሞ ታላሚውን ቋንቋ ላለመማር ሲወስኑ የሚታዩት የሚሉትን ጥያቄዎች ያነሳሉ፡፡

ምሁራኑ እንደገለፁት በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ተማሪዎችን እናገኛለን፡፡ ተማሪዎች በፆታ፣ በመልክና በእድሜ እንደሚለያዩ ሁሉ ለትምህርት አቀባበልም እንዲሁ የተለያየ ፍላጎት ተነሳሽነት አላቸው፡፡ የተወሰኑት ታላሚውን ቋንቋ ለመማር ፍላጎታቸው እጅግ የላቀ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ጨርሶ መማር የማይፈልጉም ይስተዋላሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ወይም የማስተማሪያ ዘዴው ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ Harmer (1991:5-6) እንደገለፁት ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሳየት እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

- መምህሩ ተማሪዎቹ የቋንቋ ትምህርቱን እንዲወዱ በተማሪዎች ዘንድ ሳቢ ቃላትን መጠቀም፡፡
- የቋንቋ ትምህርቱን በሚያስተምርበት ጊዜ በተማሪዎች ፊት ደስተኛ መሆን
- ለሁሉም ተማሪዎች የእውቀት አባት በመሆኑ ተማሪዎቹን በእኩል አይን መመልከት መቻል፡፡
- ወደ ክፍል በሚገባበት ሰዓት ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የሚያስችል በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቃል፡፡
- መምህሩ ስብዕናው የተከለከለ ወይም የተሟላ መሆን አለበት፡፡

ከላይ እንደተገለጸው መምህራን እነዚህንና መሰል ሁነቶችን ታሳቢ በማድረግ ታላሚውን ቋንቋ ለተማሪዎች ሊያደርሱ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የማህበረሰቡ አንድ አካል እንደመሆናቸው መጠብን የራሳቸው ፍላጎት፣ አስተሳሰብና አመለካከት እንደሚኖራቸው ይታወቃል፡፡ ቢሆንም የራሳቸውን ፍላጎትና አመለካከት የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ላይ ማንጸባረቅ የለባቸውም፡፡

Robinson (1991:80) እና Littlewood (1984) እንደገለፁት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት መምህሩ የሚያስተምረውን ቋንቋ በሚመለከት በቂ እውቀት ያለው፣ አንባቢና ተዘጋጅቶ የሚመጣ፣ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲከታተሉ የሚያደርግ ከሆነ ምንም እንኳ ተማሪዎቹ ከዚህ ቀደም ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ቅድሚያ የሚሰጡ ቢሆንም በመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ ተማርከው የቋንቋ ትምህርቱን በአግባቡ ይከታተላሉ፡፡ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ በአንፃሩ መምህሩ በቂ ዝግጅት የማያደርግ፣ የሚሳደብና የሚቆጣ፣ ለማስተማር ፍላጎት የሌለው ከሆነ ደግሞ ተማሪዎቹ ለመማር ተነሳሽነት ስለማይኖራቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ ጫና ይፈጥራሉ፡፡ የተሻለ ውጤትም ማስመዝገብ አይችሉም፡፡ በዚህም ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ያሳያሉ፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ለማጠቃለል ያህል የመምህራን መዘጋጀትና ያለመዘጋጀት፣ ፍላጎት ወይም ለማስተማር መነሳሳትና ያለመነሳሳት በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት የአቀባበል ሁኔታ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያሳያል፡፡

በHarmer (1991:4-6) አገላለፅ የማስተማሪያ ዘዴው ሲባል ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎችን ለመማር የሚያነሳሳ የሚሆንበትና የማይሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ይህም መምህራን ተማሪዎችን በማሳተፍ እንዲሁም እጅ የሚያወጡበትን ብቻ ሳይሆን የሚያወጡበትን ግንዛቤ በመውሰድ ማሳተፍ ይገባል፡፡ እንደ ርዕሱ ይዘት ሁኔታ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚያስተምሩ ከሆነ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት አሳድረው በአግባቡ ይከታተላሉ፡፡ ነገር ግን ፍዝ በሆነ መንገድ ትምህርቱን የሚያስተምሩ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ስለሚቀንስ አሉታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡

ከላይ በምሁራኑ የተገለፀው ፅንሰ ሀሳብ ለማጠቃለል ያህል መምህሩና የማስተማሪያ ዘዴው ታላሚውን ቋንቋ በሚማር ተማሪ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብር ከፍተኛ የሆነ ሚና እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህም መምህሩ ለአጠቃላይ ቋንቋ ትምህርቱን በመማር ማስተማር ሂደት የሚያከናውናቸው ልዩ ልዩ ተግባራት ማለትም በሚያስተምረው ቋንቋ ያለው የእውቀት ደረጃ፣ አጠቃላይ ስብዕናውና ለተማሪዎች ያለው የአቀራረብ ሁኔታ፣ የትምህርት አቀራረብ ስልቱ፣ የማስተማሪያ ዘዴውና አሰጣጡ ወዘተ... ታላሚውን ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የላቀ ሚና መኖሩን ያመለክታል፡፡

## 2.5.4.መማሪያ መፃህፍት

Reed & Bergemam (1995:328) እንደገለፁት መማሪያ መጻህፍት ለመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ሚና ያላቸው የክፍል ውስጥ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መጻህፍት ለረጅም ዘመናት የመማር ማስተማሩን ደረጃ ወጥነት ባለው መንገድ ለማስጠበቅ ሊያገለግሉ የቆዩ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በክፍል ውስጥ ያለውን አውድ በመወሰን የተማሪዎችን የእርስ በእርስ ግንኙነት የሚጠናከሩ ሲሆን በመማሪያ ክፍል ከተለመደ የትምህርት ጊዜ 75% እንዲሁም ከመማሪያ ክፍል ውጭ በቤት ስራ መልክ የሚሰሩ ስራዎች 25% የሚሆነውን ክንውን ከመማሪያ መጻህፍት ጋር በተለያየዘ የሚሰሩ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡

Cunningsworth (1984:63-65) እንደገለፁት መማሪያ መጽሐፍት የተማሪዎችን እድሜ፣ አካባቢ፣ ባህልና የክፍል ደረጃ መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ ባለመሆናቸው በመማር ማስተማር ሂደት የሚያደርሱት ተጽእኖ ከፍተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ የመማሪያ መጽሐፍት መምህራን፣ ወላጆችና ሌሎች ከትምህርቱ ጋር ግንኙነት ላላቸው ወገኖች ሁሉ ተማሪዎች የሚማሩትን

ትምህርት እንዲያውቁ ያግዛል፡፡ በሌላ በኩል መማሪያ መጽሀፍት ለህብረተሰቡና በተማሪ ወላጆች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢና መማሪያ ክፍል ውስጥ የተወሰነውን የትምህርት ሂደት ይፋ የሚያወጡና ህዝባዊ የሚያደርጉ መሳሪያዎችም ናቸው ይላሉ፡፡

Husen & Postleth (1994:366-70) እንደገለፁጽ መማሪያ መጽሐፍት በሚዘጋጅበት ወቅት በውስጣቸው የሚካተቱ እውቀትና ፍልስፍናቸው በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ተማሪውን ጨምሮ የታመነባቸውና ተቀባይነት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ከሀይማኖት፣ ከዘር፣ ከጎሳ፣ ከግለሰብ አመለካከት ወዘተ ሁነቶችን እንዲያሳዩ በር ይከፍታሉ፡፡ ከዚህም አልፎ ማህበረሰቡ የማይቀበላቸውን የትምህርት ይዘቶች ከተካተቱ ግጭት ይፈጥራሉ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደተረዳነው እነዚህ መጻሐፍት የአካባቢውን ወግ ልማድና ባህል ያማከሉ፤ ማህበረሰቡንም ሆነ ተማሪዎችን ግጭት ውስጥ ሊያስገቡ የሚችሉ የግለሰብ አስተያየቶችን ያካተተ መሆን የለበትም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተማሪው አመለካከት ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ስናይ፡- ወንድወሰን (1984፡20) ከዚሁ ጋር በማያያዝ ተማሪው በ2ኛ ቋንቋ የቀረበለትን ቋንቋ የሚማረው በምርጫ ማጣት ነው፡፡ ወይም በትምህርት ተቋሙና በስርዓተ ትምህርቱ የሚሰጥና መማር ስላለበት፣ ለምዝገባ ስለሚያበቃው በመሆኑ ብቻ ከሆነና ተማሪው እያደረ በትምህርቱ እየገፋ ሲሄድ ከቋንቋው ትምህርት የሚያገኘው ትምህርት ስርዓተ ትምህርቱ እየገፋ ሲሄድ ከቋንቋው ትምህርት የሚያገኘው ትምህርት ስርዓተ ትምህርቱ የነደፈውን የትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች ከማሟላት አልፎ ለወደፊት ህይወቱ ብዙም ፋይዳ እንደማይሰጠው አድርጎ ሲመለከት አመለካከቱ ዝቅ እያለ ይሄዳል፡፡ ተማሪዎች በ2ኛ ቋንቋ ለብዙ ጊዜ ተምረው የራሳቸው ብሔረሰብ ቋንቋ  እስከመርሳት የሚደርሱበት ወይም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲጠቀሙ የ2ኛ ቋንቋው ተፅዕኖ የሚደርስበት ይኖራል፡፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ የራሳቸውን ማንነት የራስ ቋንቋና ባህል ባለቤትነት ጥያቄ አንስተው ራስን መናፈቅ ሲጀምሩ ሁኔታው የተከሰተው 2ኛ ቋንቋ በደረሰባቸው ተፅዕኖ ምክንያት መሆኑን ሲረዱ የቋንቋውን ትምህርት ሊጠሉት ይችላሉ፡፡ ለቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብም የሚኖራቸው ግምት እየላላ ይሄዳል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለመዘርዘር እንደተሞከረው በተማሪዎች የ2ኛ ቋንቋን በሚማሩበት ወቅት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የተለያዩ ሁነቶች ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ አይተናል፡፡ ይህም ጓደኛ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች፣ የመማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህሩ

ስብዕናና የማስተማሪያ ዘዴው እንዲሁም ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ያለ ፍላጎቱ በምርጫ ማጣት መማርና የተማሪው ውጤት ለሚማረው ቋንቋ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብር ተጽእኖ ፈጣሪ ተላውጦዎች ናቸው፡፡

## 2.6. የአመለካከት መለኪያ ዘዴዎች

የተለያዩ ምሁራን አመለካከትን ማጥናት አስቸጋሪ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም የሰዎች ፍላጎትና ዝንባሌ ቋሚ ያለመሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ ሆኖም የትምህርት አይነትን በተመለከተ የሚቀርብ የአመለካከት መመዘኛ ፈተና ልክ እንደ ፍላጎት ወይም ንሺ መመዘኛ ሁሉ ራሱን የቻለ መመዘኛ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በታላሚው የቋንቋ ትምህርት ላይ ተመርኩዞ አመለካከትን ሊለኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በመጠየቅ ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት መመርመር ይቻላል፡፡

በGardner (1985) አገላለፅ የ2ኛ ቋንቋን በማስመልከት ተማሪዎቹ ለትምህርት ያላቸውን የአመለካከት ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የአመለካከት መመዘኛ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ የአመለካከት የመመዘኛ መስፈርቱም በተለያየ መልኩ በማቅረብ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይሄውም ባለ ሦስት ስፍረታዊ፣ ባለ አምስት ስፍረታዊ የአመለካከት መለኪያ፣ ባለ ሰባት ስፍረታዊ የአመለካከት መለኪያዎች በማሳየት በምሳሌነት አሳይቷል፡፡ ይህም ባለ ሦስት ስፍረታዊ ማለት ሦስት አማራጮችን የያዘ ሲሆን፣ ባለ አምስት ስፍረታዊ አምስት አማራጮችን የያዘና ባለ ሰባት ስፍርታዊ ደግሞ ሰባት አማራጮችን የያዘ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ Gardner (1985:2006) እንገለፁት የሰውን አመለካከት በይበልጥ አመቺ የሚሆነው ባለ ሰባቱ በተለያየ ደረጃ የመለካት አቅም ቢኖረውም ለመረጃ ሰጪዎች አመቺ የሚሆነው ግን ባለ አምስቱ እንደሆነ በመስበክ ጥናት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከባለ ሦስቱ፣ ባለ ሰባቱና ባለ አምስቱ ስፍረታዊ የአመለካከት መለኪያዎች ያለው ልዩነት ሲታይ ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑን ምሁራኑ ያስገነዘባሉ ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖችን ስለ አንድ ነገር ያላቸውን አመለካከት ለመጠየቅ እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግለን የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆን ቃለ መጠይቅንና ምልከታን ደግሞ በአጋዥነት የሚያገለግሉ ይሆናል፡፡

## 2.7. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

በዚህ ጥናት ስር ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው የቀደምት ስራዎችን መቃኘት ነው፡፡ በመሆኑም ከጥናታዊ ጽሁፌ ጋር በመጠኑ ተቀራራቢነት ያላቸው የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎችን ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ ፅሁፎች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ እንደሚከተለው እንመልከታቸው፡፡

- ታሪኩ (1988 ዓ.ም) "የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት የሚል ሲሆን የታሪኩ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚያመሳስለው በርዕሰ ጉዳዩ ማለትም ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት መፈተሽ ሲሆን በሁለቱ ጥናታዊ ፅሁፎች ማለትም በታሪኩ እና በዚህ መካከል ያለው ልዩነት ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠኚ ተማሪዎች በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ የሚማሩና  በአዲስ አበባ የሚማሩ መሆናቸው፡፡ ይህም በአዲስ አበባ የሚማሩ ተማሪዎችና በሸካ ዞን  የሚማሩ ተማሪዎች በባህላቸው፣ በአስተሳሰባቸውም የተለያዩ መሆኑ፣ በመቀጠልም የኔ ጥናትአመለካከትን ብቻ ሳይሆን አመለካልታቸው በውጤታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ስለሚዳስስ ልዩነት አላቸው፡፡ ርዕሰ ጉዳዩ የተጠናበት ጊዜ ሰፊ ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡
- ጌታቸው (1999 ዓ.ም) "በጅግጅጋ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በሶማልኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በሚል ያጠና ሲሆን ይህ ጥናትና ምርምር ከኔ ጥናት ጋር በአመለካካት ዙሪያ የተሰራ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን የእኔ ጥናት ከዚህ የሚለየው አመለካካትን ብቻ ሳይሆን አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ የሚያሳድረውን ጫና በመዳሰሱ ይለያል፡፡
- ኢዮብ ፀጋዬ(2010) ባደረጉት ጥናት በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በ2ኛ ደረጃ ት/ት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ት/ት ላይ ያላቸው አመለካካት ትንተና በሚል ርዕስያደረጉትን ጥናት የተመከትኩ ሲሆን በዚህ ጥናት አጥኚው የተጠቀሙት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ቅይጥ የጥናት ዘዴን ሲሆን በዚህም ጥናታቸው አመለካካት ስንል ሁለት ዓይነት እንደሆነና እኒህም የአመለካከት አይነቶች በጎ የሆነ አመለካካትና በጎያልሆነ አመለካካት እንዳሉና በተለያዩ ጫናዎች እንደሚፈጠሩ አሳተዋል፡፡ይህ ጥናት

ከእኔ ጥናት ጋር በአመካካት ዙሪያ መሰራቱ አንድ ቢያደርገውም የእኔ ጥናት አመለካካት በውጤት ላይ የሚያሳድረውን ጫና የሚዳስስ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያቀራርባቸው ነገር ቢኖር ሁሉም ጥናታዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አመለካከት መፈተሽ ወይም ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት መፈተሽ የሚሉ በመሆናቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የሚደረጉ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች ወጥና ሥርዓታዊ አካሄድን የተከተሉ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በጥናቱ አላማ ላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ትኩረት በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በፌዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ትንተና በሚል የቀረበ ሲሆን በዚህም የተማሪዎችን አመለካከት ይፈትሻል ፣ አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ ያሳደረውን ጫና ይመለከታል፡፡ ጥናቱ የተከተለው የአሰራር ዘዴ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን ነው፡፡

አይነታዊ የምርምር ዘዴ አንድን የተከሰተ ችግር በመፍታት እና የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ስለሚያስችል ነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተከተልኩት ስልት ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ገላጭ የምርምር ዘዴ አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቶ በገለፃ መልክ የሚያቀርብበት ዘዴ ነው፡፡

በመሆኑም እኔ ለመረጥኩት ርእሰ ጉዳይ ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ይህንን የምርምር ዘዴ ተጠቅሜያለሁ፡፡ የተማሪዎችን አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ለመዳሰስ መረጃወቹ በጽሑፍ መጠይቅ እና በፈተና ተሰብስበው መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥር የሚገልጽ ወይም መጠንን ገላጭ በመሆናቸው መረጃዎቹ የሚተነተኑት በስታቲስቲካዊ ዘዴ ስለሆነ መጠናዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጮች

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን መረጃዎቹም በዋናነት በተተኳሪው የክፍል ደረጃ የሚማሩ ማለትም በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9 ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በናሙናነት በተመረጠው በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚመለከት ነው።

### 3.3.1.የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ የፊዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው ።የተመረጠውም በአመች የናሙና ስልት ነው ።።። ምክንያቱም አጥኝው በቦታው በመምህርነት እየሰራ ያለ በመሆኑ አካባቢውንና የትምህርት ቤቱን ሁኔታ በሚገባ ማወቁ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባለማወቅ ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሰናክሎችን በተወሰነ ደረጃ መቀነስ ይቻላል ከሚል እምነት ነው። በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ለአጥኚው አመች በመሆኑ ይህትምህርት ቤት ተመርጧል።

### 3.3.2.የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው የክፍል ደረጃ የ9ኛ ክፍል ነው።ይህም የሆነበት ምክንያት በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የክፍል ደረጃወች ማለትም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ከሚገኙ ተማሪዎች ውሥጥ በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችየሚገኙት በዚሁ ክፍል በመሆኑ ክፍሉ ተመርጧል። የተመረጠውም በዓላማ ተኮር ናሙና ነው።ምክንያቱም ያለው (2001፡132) ሲገልጹ "ዓላማ ተኮር ዘዴ ለጥናቱ አላማ ስኬታማነት ይበልጥ የሚጠቅመውን አባላት በመለየት መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ ነው"። አጥኝው የአካባቢውንና የትምህርት ቤቱን ነባራዊ ሁኔታ በመመርመር ለጥናታዊ ፅሁፍ አላማ ግብ መምታት ወሳኝ መረጃ ያስገኛል ተብሎ የታሰበው የክፍል ደረጃ በናሙናነት ተመርጧል።

### 3.3.3.የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

የተማሪዎችን ናሙና አመራረጥ በተመለከተ በትምህርት ቤቱ የ9ኛ ክፍል 3 ክፍሎች ሲሆን 9ኛA፣ 9ኛB እና 9ኛC በሦስቱም ክፍል የሚገኙና አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ ተማርዎች በሙሉ ተካተዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት በጥናቱ ርዕስ መሰረት አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱእና በዘጠንኛ ክፍል ውሥጥ የሚገኙ ተካተውበታል። በዚህም ጠቅላይ የንሞና ዘዴን ተጠቅሜያለሁ።

ለጥናቱ አመቺና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም የፅሁፍ መጠይቅ እና ፈተና ናቸው፡፡በነዚህ የመረጃ ማሰባሰቢያ የተሰበሰቡት መረጃወችም በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.3.4.የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ በዋናነት የተመረጠ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ መጠይቁ የተዘጋጀው ለተማሪዎች ሲሆን የመጠይቁ መሰረታዊ አላማ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ መጠይቆቹ የተማሪዎችን አጠቃላይ ማንነት፣ የመማሪያ መፅሐፍት፣ የመምህሩ ስብዕናና የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ ቤተሰብና ጓደኞች እንዲሁም ለፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች የተመለከቱ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹም በውስጣቸው አዎንታዊ እና አሉታዊ መንፈስ ያላቸው  ሲሆን ጥያቄዎቹ የተዘጋጁትም አጥኝው የቀደምት ስራዎችን በመቃኘት እንዲሁም ያለው (2001) እና Dubin (1986)ን በመመልከት በዚያ መሰረት ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ግብ መምታት ይበጃሉ የተባሉ ጥያቄዎች ከተዘጋጁ በኋላ በመጀመሪያ በተለያዩ የቋንቋ ምሁራን በማስገምገም ለተማሪዎች በመበተን ሙከራ ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ በሙከራ ሰዓት የታዩ ድክመቶችን በማስተካከል ለአማካሪ በመስጠት በአማካሪ አስተያየት  መሰረት ተስተካክለው ተዘጋጅተዋል፡፡ እንዲሁም ከአማካሪ እና ከሌሎች ባለሙያዎች በተገኘው ምላሽ መሰረት ተተኳሪ ተማሪዎችን በሚመጥን መልኩ ባለ አራት ደረጃ ባላቸው አራት አዎንታዊ የሊከርት አጻጻፍ ስልት ተዘጋጅተዋል፡፡ በጣም እስማማለሁ 4 ነጥብ፣  እስማማለሁ 3 ነጥብ፣ በጣምአልስማማም 2 ነጥብ፣ አልስማማም 1 ነጥብ የያዘ የጽሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች ማለትም 52ቱም በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠንኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጎ ሁሉም ተሞልተው ቀርበዋል፡፡

### 3.3.5. ፈተና

ፈተና ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን ተማሪዎች በቀላሉ ተረድተው ሊመልሷቸው ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለተማሪዎች ቀርበዋል፡፡በይዘታቸውም ቢሆን የተማሪወችን አመለካከት ወደመልካም ይመራሉ የተባሉና የተማሪዎችን አቅምና ችሎታ ይመጥናሉ የተባሉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ተተኳሪ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት ፈተና እንዲወስዱ ተደርጎ መረጃው በስታቲክሳዊ ትንተና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4.1.የመረጃ ትንተና የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ መረጃዎች በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰባስበዋል፡፡ ለአተናተን እንዲሁም ለአቀራረብ ያመች ዘንድ መረጃዎቹ ለሁለት ተከፍለው ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው የቅድመና የድህረ ት/ት ፈተናዎች ትንተና የሚቀርብበት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የጽሑፍ መጠይቅ የሚተነተንበት ክፍል ነው፡፡

### 4.1.1. የቅድመ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ሠንጠረዥ-2 ከቅድመ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልዩነት**

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 12 | 40 | 26.27 | 6.846 |

በሠንጠረዥ 2 ላይ እንደምንመለከተው የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ ት/ት ፈተና ያስመዘቡት ዝቅተኛው 12 ሲሆን ከፍተኛው ውጤት ደግሞ 40 ነው፡፡ የጠቅላላ ተማሪዎች አማይ ውጤት (26.27) መደበኛ ልዩነቱ ደግሞ 6.846 ነው፡፡

### 4.1.2. ከድህረ ትምህርት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ከፍ ለማድረግና የተሸለ ውጤት ለማግኘት የቅድመ ትምህርት ፈተናዎች ሰጥቶ ደረጃ ማሳወቁ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከምንም በፊት ለተሳታፊ ተማሪዎች ቅድመ ግንዛቤ ፈተና ተሰጥቶአል፡፡

ከዚያም የተማሪዎች ግዛቤ ለማሳደግ ወይም ለተተኳሪው ቋንቋ ጥሩ አመለካት ኑሮአቸው ትምህርቱን እንዲከታተሉና ጥሩ ውጤት እነዲያስመዘግቡ ለአምስት ሳምንት ያህል ትምህርት ተሰጥቶአቸዋል፡፡ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኂላ ተማሪዎች የአመለካከት ለውጥ ማምጣቸውን ይህ አመለካከታቸው ከአሉታዊወደ አዎንታዊ መቀየሩን ለመረዳት ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሰኝጠረዥ 3 ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 18 | 52 | 33.25 | 6.738 |

ከሰንጠረዥ 3 መረዳት እንደሚቻለው የጥናቱ ተሳታፊዎች በድህረ ትምህርትፈተናው ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 18 ሲሆን ከፍተኛው ውጤት 52 ነው፡፡ የጠቅለላ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ደግሞ 33. 25 ነው፡፡ መደበኛ ልይይቱም 6.738 መሆኑ ተገልጿል፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ከድህ ረት/ት ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያነሰ ሲሆን የድህረትምህርት ፈተና ከፍተኛ ውጤት ከቅድመ ትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት የበለጠ ሆኗል፡፤ ይህም የተማሪወች አመለካከትከአሉታዎ ወደ አዎንታዊ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሁለቱ ፈተናዎችአማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩም ለመፈተሽም የዳግም ልኬታ ናሙና ቲ- ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4 ላይ ቀርቧል::

### 4.1.3. የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተናና ልዩነት በዳግም ልኬት ናሙና ተ- ቴስት

ሠንጠረዥ 4 የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና የአመለካካት መሻሻል በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | የነጻነጽ ደረጃ | የቲ ዋጋ | የጉልህት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 26.27 | 51 | 7.009 | 0.000 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | | 33.25 | | | |

በሠንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) ከቅድመ ትምህርት ፈተና አላካይ ውጤት (26፣27) ይበልጣል፡፡ በመደበኛ ልይይትም በኩል የድህረ ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይም የነሰ ቢመስልም ሁለቱም የተማሪዎች ውጤት ከአማካይ ሰፊ ልዩነት እንዳለው የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በጉለቱም አማካዮች መካከል የታየው ልዩነት በስታስቲክስ ጉልህነት ያለው ስለመሆኑ መረጋጋት ስላለበት ለዚህ ሲባል የዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በ51 የነጻነት ደረጃ (ቲ=7.009 ) የፒ ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱም አማካዮች መካል በስታስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ለውጡ ለተማሪዎች በተሰጠው የግናዛቤ ትምህርት ምክንያት የመጣ የአመለካከት ለውጥ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 4.1.4. የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

የተማሪዎች አመለካካት ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ መቀየሩን ባገኙት ውጤት መገንዘብ እነደሚቻል በ 2.4.3 ተገልጿል፡፡የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የአመለካካት ለውጥ ማለትም አመለካከታቸው ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ መቀየሩን ማወቅ ይቻል ዘንድ በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት የቀረበው ፈተና ታርሞ በእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘው ውጤት በተደምሮ ከ60% ተይዛል፡፡

ሰንጠረዥ 5 ከቅድመ ትምርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| የተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | በ% |
|---|---|---|
| 12 | 1 | 1.9 |
| 14 | 1 | 1.9 |
| 16 | 2 | 3.8 |
| 18 | 4 | 7.7 |
| 20 | 4 | 7.7 |
| 21 | 1 | 1.9 |
| 22 | 5 | 9.6 |
| 23 | 1 | 1.9 |
| 24 | 4 | 7.7 |
| 25 | 1 | 1.9 |
| 26 | 2 | 3.8 |
| 28 | 8 | 15.4 |
| 29 | 1 | 1.9 |
| 30 | 5 | 9.6 |
| 31 | 2 | 3.8 |
| 33 | 2 | 3.8 |
| 34 | 2 | 3.8 |
| 36 | 1 | 1.9 |
| 38 | 1 | 1.9 |
| 39 | 1 | 1.9 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |

ሰንጠረዥ 6› ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| የተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | በ% |
|---|---|---|
| 18 | 1 | 1.9 |
| 20 | 1 | 1.9 |
| 22 | 3 | 5.8 |
| 26 | 1 | 1.9 |
| 28 | 4 | 7.7 |
| 30 | 10 | 19.8 |
| 32 | 6 | 11.9 |
| 34 | 4 | 7.7 |
| 35 | 4 | 7.7 |
| 36 | 8 | 15.4 |
| 38 | 2 | 3.8 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| 42 | 2 | 3.8 |
| 44 | 1 | 1.9 |
| 45 | 1 | 1.9 |
| 50 | 1 | 1.9 |
| 52 | 1 | 1.9 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |
| | | |

በሰንጠረዥ 5 እና 6 የተገለጸውየተማሪዎች የውጤት ድግግሞሽ ለትንታኔ ያመች ዘንድ ወደ100% ተለውጧል፡፡ ይህንንም በሰንጠረዥ 7 ይመለከቷል፡፡

ሰንጠረዥ 7. በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| ውጤት | ቅድመ ት/ት ፈተና | | ድህረ ት/ት ፈተና | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | |
| 100-90 | 0 | 0 | 2 | 3.85 | |
| 80-70 | 5 | 9.6 | 8 | 15.38 | |
| 60-50 | 12 | 23.08 | 32 | 61.54 | |
| ከ50 በተዘች | 35 | 67.31 | 10 | 19.23 | |

በሰንጠረዥ 7. እንደተመለከተው በቅድመ ትምህርት ፈተናው ተማሪዎች ያስዘገቡት እጅግ በጣም ከፍተኛ ውጤት ( ከ90-100%) ያገኙ ተማሪዎች ብዛት 0(0%) ከፍተኛ ውጤት ከ(70-80) 5 (9.6%)፣መካለኛ ወይም (50-60%) ያገኙ ተማሪዎች 12 ወይም (23.08%)፣ ዝቅተኛ (50) በታች 35 ወይም (67.31%) ናቸው፡፡ከዚህ እንደምረዳው የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ውጤት አነስተኛ እነደሆነ ነው፡፡ይህ ደግሞ የሚያመለክተው በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በድህረ ትምህርት ፈተናው በጣም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ከ(90-100%) ያገኙ ሁለት ተማሪዎች ሲሆኑ ይህም በፐርሰንት ሲሰላ 3.85 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ማለትም ከ(70-80%) ያመጡ ተማሪዎች በቁጥር 8 ሲሆኑ ይህም በፐርሰንት ሲሰላ (15.38%) ያሳያል፡፡መካከለኛ ውጤት ያስመዘገቡት ደግሞ ማለትም (50-60%) ያመጡ ተማሪዎችብዛት በቁጥር 32 ሲሆኑ ይህንን ደግሞ በፐርሰንት ስናሰላው (61.54%)ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከ50 በታች ወይም ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን ስንመለከት በቁጥር 10 ሲሆኑ ይህንንም በፐርሰንት ስናሰላው (19.23%) ነው፡፡ይህ ውጤት የተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸሻለና እየተለወጠ መሄዱን ያሳያል፡፡ ማትም የተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ እየተቀየረና ውጤታቸውም እየተሸሻለ መሔዱን በትክክል ያሳያል፡፡

### 4.1.5. ከቅድ ት.ምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ 8 ከቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1. | አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎት አለኝ፡፡ | 7 | 13.5 | 29 | 55.8 | 12 | 23.1 | 4 | 7.7 |
| 2. | አማርኛ ትምህርት ሁልጊዜ መማር ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 9.6 | 11 | 21.2 | 21 | 40.4 | 15 | 28.8 |
| 3. | አማርኛ ፊደላት በትክክል መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 10 | 19.2 | 20 | 38.5 | 10 | 19.5 | 12 | 23.1 |
| 4. | አማርኛ በትክክል ማንበብና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 7 | 13.5 | 18 | 34.5 | 15 | 28.8 | 12 | 23.1 |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አከብራለሁ፡፡ | 7 | 13.5 | 6 | 11.5 | 27 | 51.9 | 12 | 23.1 |
| 6. | በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ኃሳብ በቀላሉ መረዳት እወዳለሁ፡፡ | 15 | 28.8 | 18 | 34.6 | 9 | 17.3 | 10 | 19.2 |
| 7. | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ አመለካከት ቢያድግ እወዳለሁ፡፡ | 9 | 17.3 | 19 | 36.5 | 11 | 21.1 | 13 | 25.0 |
| 8. | አማርኛን በትክክል መጻፍና ማንበብ እፈልጋለሁ፡፡ | 11 | 21.2 | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |
| 9. | ሁልጊዜ በአማርኛ | 11 | 21.2 | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቋንቋ መናገር እወዳለሁ። | | | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እፈልጋለሁ። | 9 | 17.3 | 5 | 9.6 | 16 | 30.8 | 22 | 36.5 |

በሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደተቻለው መጠይቁን ከሞሉት 52 ተማሪዎች መካከል በ1ኛው ጥያቆ 16 (30.8) ፡ በ3ኛው ጥያቄ 2 2(42.3) በ5ተኛው ጥያቄ 39(75.0) ፡ በ7ኛው ጥያቄ 24(46.2) ፤በ8ኛው ጥያቄ 21(40.4) በ9ኛው ጥያቄ 34( 65.4) በ10ኛው ጥያቄ 38 (73.1) ተማሪች ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካካት ዝቅተኛ መሆኑን ተረድተዋል።

#### 4.1.5.1. ከድህረ ት/ት በጹሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ 9 በድህረ ት/ት በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1. | አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎት አለኝ። | 3 | 5.8 | 16 | 30.8 | 25 | 48.1 | 8 | 15.4 |
| 2. | አማርኛ ትምህርት ሁልጊዜ መማር ደስ ይለኛል። | 5 | 9.6 | 9 | 17.3 | 22 | 42.3 | 16 | 30.8 |
| 3. | አማርኛ ፊደላት በትክክል መጻፍ | 8 | 15.4 | 10 | 19.2 | 14 | 26.9 | 20 | 38.5 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እችላለሁ። | | | | | | | | |
| 4. | አማርኛ በትክክል ማንበብና መጻፍ እችላለሁ። | 6 | 11.5 | 9 | 17.3 | 18 | 34.6 | 19 | 36.5 |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አከብራለሁ። | 9 | 17.3 | 8 | 15.4 | 24 | 46.2 | 11 | 21.2 |
| 6. | በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ኃሳብ በቀላሉ መረዳት እወዳለሁ። | 15 | 28.8 | 27 | 51.9 | 5 | 9.6 | 5 | 9.6 |
| 7. | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ አመለካከት ቢያድግ እወዳለሁ። | 7 | 13.5 | 4 | 7.7 | 12 | 23.1 | 29 | 55.8 |
| 8. | አማርኛን በትክክል መጻፍና ማንበብ እፈልጋለሁ። | 4 | 7.7 | 7 | 13.5 | 15 | 28.8 | 26 | 50.0 |
| 9. | ሁልጊዜ በአማርኛ ቋንቋ መናገር እወዳለሁ። | 6 | 11.5 | 4 | 7.7 | 14 | 26.9 | 28 | 53.8 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እፈልጋለሁ። | 21 | 40.4 | 4 | 7.7 | 8 | 15.4 | 19 | 36.5 |

ከሠንጠረዥ 9 እንደተመለከተው በጥያቄ አንድ ላይ ለቀረበው ጥያቄ የስምምነት ምላሽ የሰጡት 33 (63.5%)፣ ጥያቄ ሦስት 34 (65.4%) ጥያቄ አምስት 35 (67.4%)፣ ጥያቄ ሰባት 41 (78.8%)፣ ጥያቄ ስምንት 41 (78.8%) እና ጥያቄ ዘጠኝ 42 (80.7%) እንደሆኑ ተገልጿል። ይህም ያልተስማሙት ተማሪዎች አነስተኛ ቁጥር እንደያዙ ያመለክታል። በሌላ በኩል በተራ ቁጥር አስር ለቀረበው ጥያቄ ስምምነታቸውን የገለጹት 27 (51.9%) ናቸው። ይህም ከላይ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ከሰጡት መልስ ጋር የሚስማማ ነው።

ጥያቄ ሁለት 38 (73.1%)፣ በጥያቄ አራት 37 (71.1%)፣ ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲገልጹ፣ በጥያቄ ስድስት የስምምነት ምላሽ የሰጡት 10 (19.2%) ብቻ ነበሩ። ይህም የተማሪዎች አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ እየተቀየረ መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ ከሠንጠረዥ 8 እና 9 መመልከት እንደተቻለው በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ በተራ ቁጥር 3 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 52 ተማሪዎች መካከል 22 (42.3%) ስምምነታቸውን ሲገልጹ በድህረ ትምህርት መጠይቁ መስማማታቸውን የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር 34 (65.4%) ናቸው። ይህም የተማሪዎች አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ እየተቀየረ መሄዱን የሚያሳይ ነው። በሌላ አገላለጽ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ጥያቄ የነበራቸው አመለካከት አድጎ በድህረ ትምህርት ጥያቄ ሲሞሉ አመለካከታቸው ማደጉን ያሳያል።

በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ በተራ ቁጥር 8 በቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ወደ አሉት ያዘነበለ ነው። ምክንያቱም 31 (59.7%) አለመስማማትቸውን ሲገልጹ በድህረ ትምህርት መጠየቁ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 41 (78.8%) ስምምነታቸውን ገልፀዋል። ምክንያቱም በሌላ

በኩል በተራ ቁጥር 9 አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 42 (80.7%) ስምምነታቸውን የገለፁት በድህረ ትምህርት መጠይቁ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት በተሰጠው የግንዛቤ ትምህርት ተለውጦ ወይም ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ መቀየሩን ነው፡፡

በቅድመ ትምህርት መጠይቁ በተራ ቁጥር 5 የተሰጠው ምላሽ 24 (46.2%) በድህረ ትምህርት መጠይቁ 41 (78.8%) ስምምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል በተራ ቁጥር 10 በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ 14 (25.9%) በድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ 24 (48.1%) የሚሆኑ ምላሾች አከመስማማታቸው በተራ ቁጥር 9 ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች አመለካከት ወደ አዎንታዊ ማደጉን ጠቋሚ ነው፡፡

በተራ ቁጥር 4 በቅድመ ትምህርት መጠይቁ ተማሪዎች የሰጡት የስምምነት ምላሽ 27 (51.9%) ሲሆን በድህረ ትምህርት መጠየቁ ደግሞ 37 (71.1%) የስምምነት መልስ ሰጥተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 6 በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ መስማማታቸውን የገለፁት 19 (36.5%) በድህረ ትምህርት መጠይቁ 10 (19.2%) ናቸው፡፡ ይህም ከጥያቄ አራት መልስ ጋር ይስማማል፡፡ ምክንያቱም በቅድመ ትምህርት መጠይቁ ተመሳሳይነት ያሳያል፡:

በአጠቃላይ በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ የተሰጠው የተማሪዎች ምላሽ በአብዛኛው አለመስማማትን የሚያሳይ ነው፡፡ የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ግን መስማማት ላይ ያዘነበለ ነው፡፡ ይህም ከቅድመ ትምህርት ጥያቄ በኃላ የተሰጠው የግንዛቤ ትምህርት የተማሪዎችን አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ የቀየረና የተማሪዎች አመለካከት ማለትም በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማሪኛ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ማደጉን ያሳያል፡፡

4.1.5.3. የቅድመ እና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

ሠንጠረዥ 10፡- የቅድመ እና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| የጥያቄ አይነት | የጥያቄ ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የቲ ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | 10 | 3.36 | 0.50718 | 9 | 1.738 | 0.001 |
| ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | 10 | 3.7 | 0.33731 | 9 | 1.738 | 0.001 |

13 * P<0.05

የድህረ ጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) ከቅድመ ጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) የሚበልጥ ይመስላል፡፡ መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የቅድመ ጽሑፍ መጠይቅ ልይይት ከድህረ ጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ያነሰ መሆኑን ከሠንጠረዥ 8 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሠንጠረዥ 8 የተመለከተውን በቅድመ ጽሑፍ መጠይቅና በድህረ ጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት (Repeated sample t-test) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በ9 የነፃነት ደረጃ (ቲ-1.731) የፒ-ዋጋ (0.001) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደተቻለው የተሰጠው የግንዛቤ ትምህርት የተማሪዎችን አመለካከት ከፍ እንዳደረገ ወይም ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ የቀየረ መሆኑን ያመልክታል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው የተማሪዎች አመለከካት ዝቅተኛእንደነበረና ማለትም በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንደነበረና በተደረገው ጥናት ግን አመለካከታቸውን ብሎም ውጤታቸውን ማሳደግ እንደተቻለ አሳይቷል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የተማሪዎችን አመለካከትና የውጤት ተዛምዶ መፈተሽ ሲሆን በዚህም የተማሪዎችን አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ በመቀየር የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ

ማስቻል ነው፡፡ የነዚህንም እውንነት ለማረጋገጥ በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስና በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

በውጤት ትንተናው ሂደት በቅድሚያ የታየው ከቅድመ ትምህርት እና ከድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው መረጃ ነው፡፡

ከመረጃዎቹ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ የታየው የጥናቱ ዓላማ በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት በመፈተሽ ከውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና በማጥናት ውጤታቸውን ማሻሻል ሲሆን በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (26.27) በልጦ የተገኘው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (33.25) በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት (P< 0.05) ሆኖ በመገኘቱ የተማሪዎች አመለካከት መሻሻሉን አመላክቷል፡፡

በሰንጠረዥ 7 እንደተመላከተው በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኘው የተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ውጤት (0%) ዝቅተኛ ውጤት ደግሞ (67.31%) ነው፡፡

በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው በጣም ከፍተኛ ውጤት (3.86%) ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ ደግሞ (19.23%) መሆኑ ተገልጿል፡፡ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ምንም በጣም ከፍተኛ ውጤት ያልተመዘገበ መሆኑን ሲያሳይ በርካታ ተማሪዎችም ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ወቅት የነበረው የተማሪዎች አመለካከት ማለትም በሽኮኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የነበራቸው አመለካከት እና ውጤት ዝቅተኛ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡

የተማሪዎችን አመለካከትና ውጤት ለማሻሻል ግንዛቤ በመፈጠሩ የተማሪዎች በድህረ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ከፍተኛ መሆኑ አመላካች ነው፡፡

በስንጠረዥ 8 እና 9 እንደሚታየው ከቅድመ ጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.36) በልጦ የተገኘው የድህረ ጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.7) በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት (P< 0.05) እንዳለው ታይታል፡፡ ይህም የሚያሳየው የተማሪዎች አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አውንታዊ እንደተቀየረ መሆኑን ያሳያል፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከትና የውጤት ተዛምዶ መዳሰስ ሲሆን

በሁለቱም የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ተማሪዎቹ ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንደነበረና የሚያስመዘግቡትም ውጤት አነስተኛ እንደነበረ ከማሳየቱም በተጨማሪ በተደረገው የግንዛቤ ትምህርት አመለከካከታቸው ብሎም ውጤታቸው መሻሻሉን መረጃው አሳይቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ በፊዴ ሁለተኛ ደረጃ የሚማሩና አፋቸውንበሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት እና የውጤት ተዛምዶ ትንተና በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ዋና ዓላማውም በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠንኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ ወይም አመለካከታቸው አሉታዊ በመሆኑ ወደአውንታዊ እንዲቀየር ማድረግና ውጤታቸውን ማሻሻል እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ተጠቅሷል ::ከዚህም ባሻገር የተማሪዎች አመለካከት ምን ይመስላል? አውንታዊ ወይሥ አሉታዊ ? አመለካከታቸው ውጤታቸው ላይ ያሳደረው ጫና ምንድን ነው ?የማሉትን ጥያቄወችእንደሚመልስ በዚሁ ምዕራፍ ተጠቅሷል።

እነዚህን ዋናና ዝርዝር አላማዎች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ተካሂዷል። በመሆኑም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የጥናቱን ዋና አላማ መሠረት በማድረግ በፅሁፍ መጠይቅ፣እና በፈተና መረጃው ተሰብስቦ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገለፃና በስሌት በየፈርጃቸው ተመድበው ተተንትነዋል። ከትንተናው የተገኘው ውጤትም ለዋናና ዝርዝር አላማዎች መልስ አስገኝተዋል። ይህንንም እንደሚከተለው እንመልከት፡-

- ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው አመለካከት በጥናቱ ዳራና በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ላይ በምሁራን ሀሳብ በማስደገፍ ለመዳሰስ እንደተሞከረው “አመለካከት ከውልደት በኂላ በእድገት ሂደት የምናዳብረው የስብዕና ክፍል ነው። ይኸውም ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችንና ክስተቶችን ወዘተ የመውደድ የመጥላት፣ የመደገፍ የመንቀፍ፣ የመቅረብ የመራቅ ዝንባሌንና ስሜትን የሚያመለክት የስብዕና ዘርፍ ነው።” በመሆኑም አብዛኛዎች አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንደሆነ እና አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ እንዳደረገባቸው በተሰበሰቡት መረጃወች ተረጋግጧል።
- በ9ኛ ክፍል የሚማሩ አብዛኛዎቹ አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አሉታዊ እንደሆነ በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም በፈተና በተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። በቅድመ ትምህርች የጽሁፍ መጠይቅ

በተገኘው መረጃ መሰረት አብዛኞቹ በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ የነበራቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንደነበርና በዚህም ምክንያትው ውጤታቸውም አንሥተኛ እንደነበር ለማየት ችለናል።

- ከድህረ ትምህርት በኂላ በተሞላው የጽሁፍ መጠይቅ የተማሪዎቹ አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አወንታዊ የተቀየረ መሆኑን እና ውጤታቸው መሻሻሉን ካሥመዘገቡት ውጤት መርዳት ይቻላል። ይህንንም በሠንጠረዝ 2 እና 3 ማረጋገጥ ይቻላል። በፈተና የተሰበሰበውን መረጃ በተመለከተ የተማሪዎችን ቅድመ ፈተና ውጤት ሥንመለከት ተተኳሪ ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት የነበራቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንደነበር እና በዚህም ምክንያት አንሥተኛ ውጤት ያስመዘግቡእንደነበር ጠቋሚ ነው።ይህም የተማሪዎች አመለካከት በተደረገው የግንዛቤ ትምህርት መለወጡን የድህረ ፈተና ውጤታቸውን ማየት በቂ ነው።

## 5.2.የመፍትሄ ሀሳቦች

ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ ለሚኖራቸው አመለካከት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ጥናቱ ከዚህ በላይ በዝርዝር አሳይቷል። በዚህ መሰረት ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት፣ ለመማሪያ መጽሐፉ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች፣ ጓደኛ፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ የሚሉ የውጤት ግኝቶች በመጠይቁ መሰረት ተገኝተዋል። የተገኙትን መሰረታዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል።

- ወላጆች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበትና ታሪክ በሚያወርሱበት ጊዜ ልጆችን በወደፊት ህይወታቸው ላይ ተፅዕኖ የማይፈጥሩና አንዱን ከሌላው ለይተው ጥላቻ የሚያሳድሩበትን ሁኔታ (መንገድ) ተከትለው እንዲያድጉ ማድረግ እንዲሁም በንግድና በተለያዩ የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ ከመሻት ይልቅ ለሁሉም ነገር መሰረቱና አቅጣጫ መሪው ትምህርት መሆኑን በመረዳት ልጆቻቸው ትምህርት አፍቃሪዎች እንዲሆኑ ማበረታታት ቢችሉ፣
- የመማሪያ መጽሐፍትን ከላይ ተቀብሎ በቤተ መጽሀፍት ያለ ጥቅም በተማሪዎች እጅ ከማዋል ይልቅ የተማሪዎችን ችሎታና የመጻህፍት ይዘት በማገናዘብ ያለውን ነባራዊ ሁኔታና የመጽሀፉ ይዘት የማይጣጣም መሆኑን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅና ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ የተማሪውን ፍላጎትና ባህል ያማካለ መጻህፍትን ለተማሪዎች እንዲቀርብ ቢደረግ የሚመለከታቸው የትምሀርት ባለሙያዎች ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ከተናጋሪ ማህበረሰቡ ወግ ልማድና ታሪክ ጋር አያይዘው የፈጠሩትን ጥላቻ የሚቀይርና

ለትምህርታቸው ትኩረት የሚሰጡበትን መንገድ ካለው የአካባቢው ማህበራዊ አውድ ጋር በማያያዝ አመለካከታቸውን ሊለውጡ የሚችሉበትን ሁኔታ ቢፈጠር፣

- መምህራኑ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከመግባባት ይልቅ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚወዱበትንና ሊጠቀሙ የሚችሉበትን የማስተማሪያ ስልት በማመቻቸት በቋንቋው ትምህርት እንዲጠቀሙ ቢያደርጉ፤
- የትምህርት ቤት አስተዳደር ቋንቋው ግልጋሎት ላይ የሚውልባቸውን አውዶች በመፍጠር ኢ. አፍፊት ተማሪዎች ቋንቋውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ሲያስተላልፉ በማበረታታት ትምህርቱን እንዲወዱት ቢያደርጉ፤
    - ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች አመለካከት ወደ አዎንታዊነት እንዲቀየር የትምህርት ባለሙያዎች፣ የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ለተማሪው ፍላጎትና የእውቀት ዳራ ወይም ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እንዲሁም ለአመለካከታቸው ደጋፊ የሆኑ ነገሮችን ቢያቀርብላቸው የተሻለ ነው፡፡
    - ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ ይህንን ዝቅተኛ አመለካከት ወደ ከፍተኛ ወይም አሉታዊ የሆነውን ወደ አዎንታዊ ለመቀየር የመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀትና አቀራረብ ከተማሪዎች የስነ-ልቦና፣ የባህልና ቋንቋ የመማር አላማ ያገናዘበ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግና በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው እንዲሁም በተማሪዎች ላይ የመማር ተነሳሽነትን እንዲፈጥር አድርጎ ለማቅረብ በዝግጅቱ ወቅት ከተማሪዎችና ማህበረሰቡ ዘንድ የፍላጎት አሰሳ መረጃ ቢወሰድ፣
    - ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከተፈለገው ግብ ለማድረስ በመጀመሪያ ደረጃ የተማሪዎች ወላጆችንና የአካባቢውን ማህበረሰብ አጠቃላይ ስለ ትምህርትና ስለ ታላሚው ቋንቋ ያላቸውን ዝቅተኛ አመለካከት የሚቀይር የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በተለያየ መልኩ እንዲዳረስ ማድረግ፤
    - ሌላው ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአንድ አካባቢ የተከሰተን ችግር ለመፍታት የተካሄደ እንደመሆኑ መጠን የታሰበውን አላማ ከግብ ለማድረስ ችግሩን ለመፍታት ጥናታዊ ፅሁፍ በቤተ መጽሐፍ ወይም በአንድ በተወሰነ ቦታ ብቻ የሚቀመጥ ከሆነ ለአንድ ጥናትና ምርምር ለሚያካሂድ ሰው እንደ መነሻ ከመሆን ባሻገር ችግሩን ሊፈታ አይችልም፡፡ በመሆኑም ጥናታዊ ፅሁፉ ከተጠናቀቀና ማስረጃ አዘል የሆኑ ውጤቶችን

ከተገኙ በኂላ ይህን ችግር ለመፍታት ይችላል ወይም ይመለከተዋል ለተባለ አካል በአካባቢው ለሚገኘው የዞን ወይም የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የጥናታዊ ፅሁፉ ኮፒ እንዲደርሰው በማድረግና የጥናቱን ውጤቶች (ግኝቶች) በማመላከት ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ እንዲያመቻች ቢደረግ፣

- መምህራን ተማሪዎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚያስተምሩትን ይዘት ከተማሪዎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር ቢያዛምዱ
- መምህራን ተማሪዎችን በሚፈትኑበት ጊዜ በተቻለ አቅም ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉትን ቃላትናሀረጋት ቢጠቀሙ
- በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በእረፍትና ውጭ በሚጫወቱበት ጊዜ ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በመነጋገር እናበመጫወት ልምምድ ቢያደርጉ፡፡

በአጠቃላይ አፋቸውን በሸኮኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አሉታዊ እንደሆነና በዚህም ምክንያት ዝቅተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ተረጋግጧል ፡፡ በተማሪዎች የቋንቋ አመለካከት ላይም የመማሪያ መጽሐፍ፣ ጓደኛ፣ ቤተሰብና ማህበረሰቡ እንዲሁም ፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ያሳደሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በታላሚው የጥናት አካባቢ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ከመቅጠር በፊት ለመማር ማስተማሩ ውጤታማነት ወይም ግብ መምታት እንዲረዳ ችግሮችን በሚመለከተው አካል በኩል መፍታቱ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን የሚገባው መሆኑን እጠቁማለሁ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ታሪኩ (1988 ዓ.ም) "የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት የሚል ሲሆን /" አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። /ያልታተመ/

ኢዮብ ፀጋዬ(2010) ባደረጉት ጥናት በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ በ2ኛ ደረጃ ት/ት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ት/ት ላይ ያላቸው አመለካካት ትንተና በሚል ርዕስያደረጉትን ጥናትበቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። /ያልታተመ/

ጌታቸው (1999ዓ.ም) "በጅግጅጋ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በሶማልኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በሚል ያጠና ሲሆን ይህ ጥናት በቋንቋዎች ተቋም ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። /ያልታተመ/

ያለው እነዳወቅ (2001)የምርምር መሰረታዊ አተገባባር (ሁለተኛ እትም) አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

Aggrawal, J.C. (1998) *Essential of Educational Psychology* (Reprinted), New Delhii፡ Yakas Publishing House Put Ltd.

Brown, Douglas H (2007). *Principle of language learning and teaching.* Sanfrancisco State of University: Pearsan Longman.

(1994). *Principles of language learning and teaching*. New York: Prentice Hall.

Celce-Murcia, M. (1991). *Teaching English as second language or Foreign Language,* Publishing House. PVT, Ltd.

Cook, V. (1991) *Second Language learning and language teaching*: London: Eduward Arnold.

Cunningworth. (1987). *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials*. London: Biddles Ltd.

Dubin, Fraida and Elite Olshetain. (1986) *Course Dessign.* Cambridge: Cambridge University Press.

Fasold, R. (1984). "The Socio linguistic of Society". Oxford: Black well Ltd.

Gagne, R.M (1976). *The condition of learning*. New York: Halt Rinehant and Winston.

Gardner, R.C (1985). *Social psychology and Second Language Learning*. The Role of Attitude and motivation London. Edward Arnoled, Ltd.

(2006). "The Socio-Educational Model of Second Language Acquisition A research Paradigm". In S.H. Faster, Cohen, M. Medved Khajnovic, & Lj. Mihalievc Djjgunovic (Eds), *Eurosla Year Book*, 6 Amsterdam, John Benjamins Publishing Company.

Harmer, Jermy (1983). *Fundamental concepts of language teaching.* Oxford: Oxford University Press. (1991). *Handbook of language Teachers. The practice of English language teaching* (New Education) New York: Longman.

Hoffmann, C. (1995). *An Introduction to Bilingualism* London: Longman Group Uk Ltd.

Hurlock, E.B. (1996). *Developmental Psychology, A Life Span Approach*. New Delhii: Megaraw, HallPublishing Company Ltd.

Husen and Pastleth led (1994). "The International Encyclopedia of Education, 2nd Vol 1p, 535.

Krashen. S.D (2009). *Principles and Practice in Second Language Acquisition.* New York & London: Phoenix ELT.

Kuppuswamy, B. (1984). *Advanced Educational Psychology*. New Delhiin Steriling Mublishes, Private. Ltd.

Lightbown, P.M (2011). *How Language are learned*. Oxford University Press.

Lttlwood, Willian, (1984). *Foreign and second language learning: Language Acquisition research and It's Implication for the classroom*". Cambridge: CUP.

Malim, T & Ann Birtch, E.C. (1998) *Introductory Psychology*. London: Macmillan Press Ltd.

Masgort, M.A and R.C Gardner (2003) "Attitude, motivation and second language learning: A Meta-Analysis of Studies counted by, Gardner and Associates". *Language learning A journal of Research In a Language Studies*. Vol 53, No 1 PP 123-159.

McGrotty, N (1996) "language, Attitude, Motivation And Standards" In S.L Mckay and N.H. Harnberger (Eds.) *Social Linguistic and Language Teaching*. Cambridge: CUP.

McKay, S. and HornBerger (1996) *Scoial Lingustic and Language Teaching* London: Biddles Ltd.

Mehrens, W.A and Lehmann, (1984) *Measurement and Evaluation in Education and Psychology* (3rd ed.) New York: Holt, Rine hart and Winstan.

Morgan, Clifford T. (1986). *Introduction to psychology*. New York: MC Graw Hill Book Company.

Oppenheim A.N (1984). *Questionnaire Design and Attitude Measurement*. London: Gower Publishing Company Ltd.

Reed, Arthea J.S and Verna E. Bergemann. (1995). *In the classroom An Introduction to Education 2nd ed.* New York: The Dushkin Publishing Group. Inc.

Robinson, C. Paulin (1991) ESP Today: *A Practioner's Guide*: London: Printice Hall International, Ltd.

Ronsnebereg and Hawland. (1980) "Cognitive, Affective and behavioral components of Attitude" In M.J Rasenberg et al (eds.) Attitude organization and change (pp 48-64) west part connectiscuti

Russell, L. (1989). Development attitude and Attitude, interests, and values In Skinner, C.E (ed.) Educational psychology. New delhi: Prentice. Hall of India (375-83)

Skinner, E.C (1985). *Educational Psychology*. 4th ed. New York: Prentice Hall, Inc,

Smith, Alfred (1971). *The Importance of Attitude in foreign language learning.* The modern language Journal, Volss, No 2. PP.

Spolsky. B. (1998). *Condition for Second Language learning*. New York: Oxford University Press.

# አባሪዎች

**አባሪ አንድ**

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አባሪ አንድ

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 12 | 40 | 26.27 | 6.846 |

**ሠንጠረዥ-2 ከቅድመ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልዩነት**

አባሪ ሁለት

ቅድመ ትምህር ፈተና

በሸኮኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች የቀረበ ፈተና

ትዕዛዝ 1.

የሚከተሉትን ጥያቄ በማንበብ ትክክል ሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ

1.ባህላዊ ሽምግልና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላላፈ የመጣ የህብረተሰብ ሃብ ነው ፡፡

2.አየለ አዲስ መኪና ገዛ ፡፡ በዚህ ዓርፍተ ነገር ውስጥ የስል ገላጩ ገዛ የሚለው ነው፡፡

3.እኔ የሚለው ተውላጠ ስም 2ተኛ መደብ ነው፡፡

4. 3ተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች ውስጥ አንዱ እናንተ የሚለው ነው፡፡

5. መምህሩ ተማሪዎችን ተቆጣጠረ፡፡በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ሊሆን የሚችለው ተማሪዎችን የሚለው ነው፡፡

6. በአንድ የተሟላ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ሀረጎችን እናገኛለን፡፡

7. በአማርኛ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር ህግ መጀመሪያ የሚመጣው የዓረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ ወይም ግስ ነው፡፡

ትዕዛዝ 2.

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ጻፉት

1.ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የሚችል የቋንቋ ክፍል ምን ይባላል

ሀ. ቃል ለ.መደብ ሐ. ምዕላድ መ. ስም

ከሚከተሉት ውስጥ የዓረፍተ ነገር ክፍል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. መልስ የለውም

ከሚከተሉት ውስጥ ምዕላድ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ላም ለ.ኦች ሐ. -አቸው መ. ላሞቻቸው

አንበሳ ነብርን ገደለ፡፡ በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ተሳቢ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው

ሀ. አንበሳ ለ. ነብር ሐ. ገደለ መ/ሁሉም

12. በጣት የሚቆጠሩ ሲባልም ማለት ነው?

ሀ. ጣት ላይ ያሉ ለ.በቁጥር ጥቂት የሆኑ ሐ. ብዙ መ. መልስ የለም

13. ሆደ ሰፊ ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ቻይ ለ. ትስተኛ ሐ. ሰፊ ሆድ ያለው መ. ሀ እና ለ

14. እጅ አጠረው ሲል፡ ሀ. ገንዘብ አጣ ለ. እጁ ትንሽሆነ ሐ. እጁ ትልቅ ሆነ መ.ሁሉም

15.አየለ ምሳውን በላ፡፡ በዚህ ዓ. ነገር ውስጥ የዓ.ነገሩ ተሳቢ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. አየለ ለ. ምሳውን ሐ. በላ መ. መልስ የለም

ትዕዛዝ. 3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው አጭር መልስ ስጡ

16. በተሳቢነትና በባለቤትነት የሚያገለግለው የቃል ክፍል ም ን በመባል ይታወቃል?

17. ራሳቸውን የቻሉ ነገር ግን ከሌላውጋር ግንኙነት ያላቸውን ዓ.ነገሮች ለመለየት የሚያገለግል ስርዓተ ነጥብ ምን ይባላል?

18. በውስጡ ከአልድ በላይ ግሶችን የያዘ የዓ.ነገር አይነት ምን ይባላል?

19. ሆድና ጀርባ ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍች ስጡ፡፡

20. አቤል ጎበዝ ተማሪ ነው ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ቅጽል ሊባል ቃል የቱ ነው?

አባሪ ሶስት

ሰኝጠረዥ 3 ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፣ዝቅተኛ፣አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 18 | 52 | 33.25 | 6.738 |

አባሪ አራት

ድህረ ትምህር ፈተና

ሠንጠረዥ 4 የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተና የአመለካካት መሻሻል በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| የፈተና ዓይነት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | የነጻነጽ ደረጃ | የቲ ዋጋ | የጉልህት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 52 | 26.27 | 51 | 7.009 | 0.000 |

በሽኮኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች የቀረበ ፈተና

ትዕዛዝ 1.

የሚከተሉትን ጥያቄ በማንበብ ትክክል ሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ

1.ባህላዊ ሽምግልና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላላፈ የመጣ የህብረተሰብ ሃብ ነው

2.አየለ አዲስ መኪና ገዛ ። በዚህ ዓርፍተ ነገር ውስጥ የስል ገላጬ ገዛ የሚለው ነው።

3.እኔ የሚለው ተውላጠ ስም 2ተኛ መደብ ነው

4. 3ተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች ውስጥ አንዱ እናንተ የሚለው ነው።

5. መምህሩ ተማሪዎችን ተቆጣጠረ።በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ሊሆን የሚችለው ተማሪዎችን የሚለው ነው።

6. በአንድ የተሟላ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ሀረጎችን እናገኛለን፡

7. በአማርኛ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር ህግ መጀመሪያ የሚመጣው የዓረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ ወይም ግስ ነው፡፡

ትዕዛዝ 2.

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ጻፉት

1.ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሽን የሚችል የቋንቋ ክፍል ምን ይባላል

ሀ. ቃል ለ.መደብ ሐ. ምዕላድ መ. ስም

ከሚከተሉት ውስጥ የዓረፍተ ነገር ክፍል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅጽል መ. መልስ የለውም

ከሚከተሉት ውስጥ ምዕላድ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ላም ለ.ኦች ሐ. -አቸው መ. ላሞቻቸው

አንበሳ ነብርን ገደለ፡፡ በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ተሳቢ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው

ሀ. አንበሳ ለ. ነብር ሐ. ገደለ መ/ሁሉም

12. በጣት የሚቆጠሩ ሲባልም ማለት ነው?

ሀ. ጣት ላይ ያሉ ለ.በቁጥር ጥቂት የሆኑ ሐ. ብዙ መ. መልስ የለም

13. ሆደ ሰፊ ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ቻይ ለ. ትስተኛ ሐ. ሰፊ ሆድ ያለው መ. ሀ እና ለ

14. እጅ አጠረው ሲል፡ ሀ. ገንዘብ አጣ ለ. እጁ ትንሽሆነ ሐ. እጁ ትልቅ ሆነ መ.ሁሉም

15.አየለ ምሳውን በላ፡፡ በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ የዓ.ነገሩ ተሳቢ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. አየለ ለ. ምሳውን ሐ. በላ መ. መልስ የለም

**ትዕዛዝ. 3**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው አጭር መልስ ስጡ**

16. በተሳቢነትና በባለቤትነት የሚያገለግለው የቃል ክፍል ም ን በመባል ይታወቃል?

17. ራሳቸውን የቻሉ ነገር ግን ከሌላው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ዓ. ነገሮች ለመለየት የሚያገለግል ስርዓተ ነጥብ ምን ይባላል?

18. በውስጡ ከአልድ በላይ ግሶችን የያዘ የዓ.ነገር አይነት ምን ይባላል?

19. ሆድና ጀርባ ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍች ስጡ

20. አቤል ጎበዝ ተማሪ ነው። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ቅጽል ሊባል ቃል የቱ ነው ሰንጠረዥ 5 ከቅድመ ትምርት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞ

| የተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | በ% |
|---|---|---|
| 12 | 1 | 1.9 |
| 14 | 1 | 1.9 |
| 16 | 2 | 3.8 |
| 18 | 4 | 7.7 |
| 20 | 4 | 7.7 |
| 21 | 1 | 1.9 |
| 22 | 5 | 9.6 |
| 23 | 1 | 1.9 |
| 24 | 4 | 7.7 |
| 25 | 1 | 1.9 |
| 26 | 2 | 3.8 |
| 28 | 8 | 15.4 |
| 29 | 1 | 1.9 |
| 30 | 5 | 9.6 |
| 31 | 2 | 3.8 |
| 33 | 2 | 3.8 |
| 34 | 2 | 3.8 |
| 36 | 1 | 1.9 |
| 38 | 1 | 1.9 |
| 39 | 1 | 1.9 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |

ሰንጠረዥ 6› ከድህረ ት/ት ፈተና የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| የተማሪዎች ውጤት | ድግግሞሽ | በ% |
|---|---|---|
| 18 | 1 | 1.9 |
| 20 | 1 | 1.9 |
| 22 | 3 | 5.8 |
| 26 | 1 | 1.9 |
| 28 | 4 | 7.7 |
| 30 | 10 | 19.8 |
| 32 | 6 | 11.9 |
| 34 | 4 | 7.7 |
| 35 | 4 | 7.7 |
| 36 | 8 | 15.4 |
| 38 | 2 | 3.8 |
| 40 | 2 | 3.8 |
| 42 | 2 | 3.8 |
| 44 | 1 | 1.9 |
| 45 | 1 | 1.9 |
| 50 | 1 | 1.9 |
| 52 | 1 | 1.9 |
| አጠቃላይ | 52 | 100.0 |

አባሪ

ሰንጠረዥ 7. በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኘ የውጤት ድግግሞሽ

| ውጤት | ቅድመ<br>ት/ት<br>ፈተና | | ድህረ<br>ት/ት<br>ፈተና | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | |
| 100-90 | 0 | 0 | 2 | 3.85 | |
| 80-70 | 5 | 9.6 | 8 | 15.38 | |
| 60-50 | 12 | 23.08 | 32 | 61.54 | |
| ከ50 በታች | 35 | 67.31 | 10 | 19.23 | |

ሰንጠረዥ 8 ቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1. | አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎት አለኝ፡፡ | 7 | 13.5 | 29 | 55.8 | 12 | 23.1 | 4 | 7.7 |
| 2. | አማርኛ ትምህርት ሁልጊዜ መማር ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 9.6 | 11 | 21.2 | 21 | 40.4 | 15 | 28.8 |
| 3. | አማርኛ ፊደላት በትክክል መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 10 | 19.2 | 20 | 38.5 | 10 | 19.5 | 12 | 23.1 |
| 4. | አማርኛ በትክክል ማንበብና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 7 | 13.5 | 18 | 34.5 | 15 | 28.8 | 12 | 23.1 |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አከብራለሁ፡፡ | 7 | 13.5 | 6 | 11.5 | 27 | 51.9 | 12 | 23.1 |
| 6. | በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ኃሳብ በቀላሉ መረዳት እወዳለሁ፡፡ | 15 | 28.8 | 18 | 34.6 | 9 | 17.3 | 10 | 19.2 |
| 7. | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ አመለካከት ቢያድግ እወዳለሁ፡፡ | 9 | 17.3 | 19 | 36.5 | 11 | 21.1 | 13 | 25.0 |
| 8. | አማርኛን በትክክል መጻፍና ማንበብ | 11 | 21.2 | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እፈልጋለሁ፡፡ | | | | | | | | |
| 9. | ሁልጊዜ በአማርኛ ቋንቋ መናገር እወዳለሁ፡፡ | 11 | 21.2 | 20 | 38.5 | 9 | 17.3 | 12 | 23.1 |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እፈልጋለሁ፡፡ | 9 | 17.3 | 5 | 9.6 | 16 | 30.8 | 22 | 36.5 |

በሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደተቻለው መጠይቁን ከሞሉት 52 ተማሪዎች መካከል በ1ኛው

ሰንጠረዥ 9 በድህረ ት/ት በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1. | አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎት አለኝ፡፡ | 3 | 5.8 | 16 | 30.8 | 25 | 48.1 | 8 | 15.4 |
| 2. | አማርኛ ትምህርት ሁልጊዜ መማር ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 9.6 | 9 | 17.3 | 22 | 42.3 | 16 | 30.8 |
| 3. | አማርኛ ፊደላት በትክክል መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 8 | 15.4 | 10 | 19.2 | 14 | 26.9 | 20 | 38.5 |
| 4. | አማርኛ በትክክል ማንበብና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 6 | 11.5 | 9 | 17.3 | 18 | 34.6 | 19 | 36.5 |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ | 9 | 17.3 | 8 | 15.4 | 24 | 46.2 | 11 | 21.2 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አከብራለሁ፡፡ | | | | | | | | |
| 6. | በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ኃሳብ በቀላሉ መረዳት እወዳለሁ፡፡ | 15 | 28.8 | 27 | 51.9 | 5 | 9.6 | 5 | 9.6 |
| 7. | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ አመለካከት ቢያድግ እወዳለሁ፡፡ | 7 | 13.5 | 4 | 7.7 | 12 | 23.1 | 29 | 55.8 |
| 8. | አማርኛን በትክክል መጻፍና ማንበብ እፈልጋለሁ፡፡ | 4 | 7.7 | 7 | 13.5 | 15 | 28.8 | 26 | 50.0 |
| 9. | ሁልጊዜ በአማርኛ ቋንቋ መናገር እወዳለሁ፡፡ | 6 | 11.5 | 4 | 7.7 | 14 | 26.9 | 28 | 53.8 |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እፈልጋለሁ፡፡ | 21 | 40.4 | 4 | 7.7 | 8 | 15.4 | 19 | 36.5 |

ሠንጠረዥ 10፡- የቅድመ እና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| የጥያቄ አይነት | የጥያቄ ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነፃነት ደረጃ | የቲ ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | 10 | 3.36 | 0.50718 | 9 | 1.738 | 0.001 |
| ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | 10 | 3.7 | 0.33731 | 9 | 1.738 | 0.001 |

13 * P<0.05

## በተማሪዎች የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች የዚህ መጠይቅ አላማ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና በማጥናት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከተፈለገው ግብ ሊደርስ የሚችለው ትክክለኛ መረጃዎች ተሰብስበው ሲጠናቀሩ ብቻ ነው፡፡ በአጥኚዋ በኩል የተማሪዎች ምላሽም ሆነ አስተያየት በምስጢር የሚያዝ ስለሆነ ትክክለኛውን መረጃ እንድትሰጥ/ እንድትሰጭ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ውድ የሆነ ጊዜህ/ሽን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበርከኝ/ሽኝ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስህ/ሽ፡፡

**ማሳሰቢያ፡ መጠይቁ ሲሞላ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡**

**መመሪያዎች፡-**

1. አማራጭ መልሶች በቀረቡበት ቦታ ላይ ከምትመርጡት መልስ ስር ባለው ሳጥን ውስጥ የስምምነት ምልክት የሆነውን “X” ምልክት አድርጉ፡፡
2. ረጋ ብላችሁ ካነበባችሁ በኋላ
   - 2.1. በሀሳቡ ሙሉ በሙሉ የምትስማሙ ከሆነ “በጣም እስማማለሁ” በሚለው አማራጭ ስር ባለው ሳጥን ውስጥ X አድርጉ፡፡
   - 2.2. በመጠኑ ከሆነ “እስማማለሁ” በሚለው ሳጥን ውስጥ X አድርጉ፡፡
   - 2.3. በሀሳቡ የምትጠራጠሩ ከሆነ “መወሰን ያስቸግረኛል” በሚለው X አድርጉ
   - 2.4. ሀሳቡን የማትቀበሉት ከሆነ “አልስማማም” በሚለው ሳጥን X አድርጉ
   - 2.5. በሀሳቡ በጭራሽ የማትስማሙ ከሆነ “ፍፁም አልስማማም” በሚለው ሳጥን ውስጥ X ምልክት አድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | ምሳሌ | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፍጹም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ብዙ ቋንቋዎችን ማወቅ ደስ ይለኛል | X | | | | |
| 2. | ብዙ ከማዳመጥ ብዙ መናገር ይሻላል | | | | X | |

**ለተማሪዎች  የሚቀርብ የፅሁፍ መጠይቅ**

**ማሳሰቢያ፡- መጠይቁ ሲሞሉ ስም መጻፍ አያስፈልግም**

| ተ.ቁ | 1) የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካከት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የአማርኛ ቋንቋ ለመማር ፍላጎት አለኝ | | | | | |
| 2. | የአማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ደስ ይለኛል | | | | | |
| 3. | የአማርኛ ቋንቋ በትክክል መፃፍ አልችልም | | | | | |
| 4. | ግድ ሆኖብኝ እንጂ የአማርኛ ቋንቋ መማር አልፈልግም | | | | | |
| 5. | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አከብራለሁ | | | | | |
| 6. | የአማርኛ ቋንቋ መፅሀፍና ደብተር የለኝም | | | | | |
| 7. | የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ቢያመልጠኝ አልፈልግም | | | | | |
| 8. | የአማርኛ ቋንቋ በጣም ከባድና ውስብስብ ስለሆነ መማር አልፈልግም፡፡ | | | | | |
| 9. | የአማርኛ ጽሁፎችን ማንበብ እፈልጋለሁ | | | | | |
| | **2) የመማሪያ መጻሕፍት** | | | | | |
| 1. | የአማርኛ መጽሐፍ የመማር ፍላጎት እንዲኖረኝ አድርጓል፡፡ | | | | | |
| 2. | የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ አዘገጃጀት ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡ | | | | | |
| 3. | የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የተማሪዎችን ባህል ያማከለ ነው፡፡ | | | | | |
| 4. | መጽሀፉ የመናገርና መጻፍ ችሎታዬን አዳብሮልኛል | | | | | |
| 5. | አሁን ያለው የመማሪያ መጽሀፍ ቢሻሻል የመማር ፍላጎቴ ይነቃቃል፡፡ | | | | | |
| | **3) የመምህሩ ስብዕናና የማስተማሪያ ዘዴዎች** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መምህራን የሚያዘጋጁት የአማርኛ ፈተና ከተማርነው ጋር ስለማይገናኝ ውጤታችን ዝቅተኛ ነው፡፡ | | | | | |
| 2. | መምህራችን የሚሰጡትን የቤት ስራ ስለሚያርሙልኝ ከስህተቴ ለመማር ይረዳኛል | | | | | |
| 3. | መምህራናችን የሚሰጡትን የቤት ስራ እሰራለሁ | | | | | |
| 4. | የአማርኛ ትምህርትን የምወደው መምህራችንን ስለምወደው ነው | | | | | |
| 5. | መምህራናችን የተማርነውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ያስተምራሉ | | | | | |
| 6. | የአማርኛ መምህራችን የማስተማሪያ ስልታቸው ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ነው፡፡ | | | | | |
| 7. | መምህራናችን ከመጽሀፉ ውጭ ያስተምራሉ | | | | | |
| 8. | መምህራናችን ክፍለ ጊዜውን ያስተምራሉ | | | | | |
| 9. | መምህራናችን ከተማሪዎች ጋር አይግባቡም | | | | | |
| | **4) ጓደኛ፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰብ** | | | | | |
| 1. | ቤተሰቦች የአማርኛ ትምህርትን እንድማር ያበረታቱኛል፡፡ | | | | | |
| 2. | ቤተሰቦች ለቋንቋውም ሆነ ተናጋሪ ማህበረሰቦች ጥሩ አመለካከት የላቸውም | | | | | |
| 3. | ቤተሰቦች የአማርኛ ቋንቋ እንድማር አይፈልጉም | | | | | |
| 4. | የአካባቢው ማህበረሰብ የአማርኛ ቋንቋ መማር ጥቅም እንዳለው ይናገራል፡፡ | | | | | |
| 5. | ጓደኞች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት አይሰጡም፡፡ | | | | | |
| 6. | የአካባቢው ማህበረሰብ የአማርኛ ቋንቋን ይጠቀማል፡፡ | | | | | |
| 7. | የአካባቢው ማህበረሰብ የአማርኛ ቋንቋን እንድማር ያበረታቱኛል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8. | ጓደኞች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን አያከብሩም | | | | | |
| | 5) **ፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች** | | | | | |
| 1. | በአማርኛ ቋንቋ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር መግባባት ስለሚችል መማር እፈልጋለሁ | | | | | |
| 2. | የአማርኛ ቋንቋ የጨቃኝ ማህበረሰብ ቋንቋ ስለሆነ መማር አልፈልግም | | | | | |
| 3. | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ባህል ስለምጠላው ቋንቋውን መማር አልፈልግም | | | | | |

1. ፆታ ________ 2. ዕድሜ __________ 3. የክፍል ደረጃ ________________

**መመሪያ ሦስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያለህን/ሽን አስተያየት ግለጽ/ጭ**

1. ለአማርኛ ቋንቋ ጥሩ አመለካከት ከሌለህ/ሽ ቋንቋውን እንድትጠይው/እንድትጠላው ያረጉት ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
2. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ለመምህሩና ማስተማሪያ ዘዴው ያለህን/ሽን አጠቃላይ አስተያየት ፃፊ/ፍ?
3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመማር ማስተማር ሁኔታው ምን ይመስላል?

## አባሪ ሁለት

## የክፍል ምልከታ ቅጽ

በሶማሌ ክልል ሸበሌ ዞን ጎዴ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት የሚማሩ ኢ.አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሽ የተዘጋጀ የምልከታ ቅጽ

ቀን ____________________ የትምህርት አይነት _______

የት/ቤቱ ስም ____________ ክፍለ ጊዜ፡ ______________

**ክፍል አንድ፡- የተማሪዎች ሁኔታ**

1.1. የተማሪዎች የደብተርና መማሪያ መጻሕፍ አያያዝ ሁኔታ

1.2. ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ላይ ያላቸው ተሳትፎ

1.3. ተማሪዎች ለመምህሩና የትምህርት አቀራረቡ ያላቸው አስተያየትና አቀባበል

1.4. መማሪያ ክፍሉ፣ የትምህርቱ ይዘትና የመምህሩ አቀራረብ ለተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ያለው ሚና

1.5. የተማሪዎች ስነ ስርዓት አጠባበቅ ሁኔታ

1.6. ተማሪዎች ለእለቱ ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት

1.7. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመቀበል እና የመተግበር ፈቃደኝነት

1.8. የተማሪዎች ብዛትና የአቀማመጥ ሁኔታ

**ክፍል ሁለት፡- የመምህራን የክፍል አያያዝና የትምህርት አቀራረብ ሁኔታ፣**

2.1. መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት

2.2. የይዘት አሳታፊነት፣ ለተማሪዎች ያላቸው እይታና አሳታፊነት

2.3. መምህራን ተማሪዎችን የመቆጣጠርና የክትትል ሁኔታ

2.4. መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ያለው አቀራረብና መስተጋብር

2.5. ክፍለ ጊዜውን በአግባቡ የመጠቀም ሁኔታ

2.6. መምህሩ ለሙያውና ለሚያስተምረው የቋንቋ ትምህርት ያለው ፍላጎት

## አባሪ ሦስት

**ለተማሪዎች የቀረበ ቃለ መጠይቅ**

1. ወላጆች ስለ አማርኛ ቋንቋ ምን አይነት አስተያየት ይሰጡሃል/ሻል?
2. በዚህ ት/ቤት የሚማሩ ኢ-አፍ- ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በተገቢ ሁኔታ ይማራሉ ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?
3. መምህሩ በሚያስተምሩበት ሰዓት ሁሉም ተማሪዎች ይሳተፋሉ?
4. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?
5. ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አስተያየት ምን ይመስላል? እንድትማር/ሪ ያበረታታሉ?
6. የመማሪያ መጻሕፍትና መምህሩ ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲማሩ የሚገፋፉ ናቸው?
7. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ይገኛሉ?
8. መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት ይጠብቃሉ?

# አባሪ አራት

## ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

1. ተማሪዎችዎ ለአማርኛ ቋንቋ ምን አይነት አመለካከት አላቸው?
2. የተማሪዎችዎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀባበል ሁኔታ ምን ይመስላል?
3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ሂደት ላይ ምን ምን ችግሮች ይታያሉ?
4. የመማሪያ መጻሕፍት ከተማሪዎች የመማር ባህል ጋር ተያያዥነት አላቸው?
5. በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያላቸው የቋንቋው የአጠቃቀም ሁኔታ ምን ይመስላል?
6. በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሁኔታ ላይ ወላጆችና የት/ቤቱ አስተዳደር ያላቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል?
7. ተማሪዎችዎ በታላሚው ቋንቋ ማንበብ ይችላሉ?
8. ተማሪዎችዎ የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችን ያከብራሉ?
9. ተማሪዎችዎ ሀሳባቸውን በታላሚው ቋንቋ በመጻፍ እና በመናገር የመግለጽ ሁኔታ ምን ይመስላል?